# ፀረ-ሙስና

ፀረ–ሙስና ቅጽ 1 ቁጥር 7 ጥር 2015 ዓ.ም


## በአለም ባንክ የገንዘብ ድጋፍ በሚሰሩ ፕሮጅክቶች በተደረገ የማጣራት ስራ በአፈፃፀም ሪፖርት ላይ ውይይት ተካሄደ

ኮሚሽኑ የ2015 ዓ.ም የመጀመሪያ በጀት ዓመት በሀገር አቀፍ ደረጃ በአለም ባንክ የገንዘብ ድጋፍ የሚሰሩ ፕሮጅክቶችን የማጣራት ስራ በማካሄድ በአፈፃፀም ሪፖርት ላይ በማጣራት ስራው ከተሰማሩ 70 አመራርና ባለሙያዎች በተገኙበት በሂልተን ሆቴል ውይይት ተካሂዷል፡፡

የማጣራት ስራው በዋናነት የተደረገው ፕሮጀክቱን በሚመሩት በገንዘብ ሚኒስቴር፣ በግብርና ሚኒስቴር፣ በጤና ሚኒስቴር፣ በውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር፣ በከተማና ከመሰረተ ልማት ሚኒስቴር እና በኢንቨስትመንት ኮሚሽን ተቋማት ነው፡፡

የማጣራት ስራውም በቀረቡ ሪፖርቶች መነሻነት የሪፖርቱን ትክክለኛነት፣ በቀረቡ ጥቆማዎች ላይ የተወሰዱ አስተዳደራዊና ህጋዊ ዕርምጃዎች መወሰዱን፣ ፕሮጀክቱ ከሙስናና ብልሹ አሰራር የፀዱ መሆናቸውን እና በተቋማቱ የስነ ምግባርና የፀረ-ሙስና ባለሙያ እንዲሁም የፕሮጀክቱ አስተባባሪ ባለሙያ መደመደቡን በማረጋገጥ መከናወኑን ከመድረኩ ተጠቁሟል፡፡

በሰባት የፕሮጀክት ዘርፎች በተደረገው የማጣራት ስራ መነሻነትም በስራው በተሰማሩ ሃላፊዎች አማካኝነት ለተሳታፊዎች ሪፖርቱ ቀርቦ ውይይት በማድረግ የጋራ ተደርጓል፡፡

የፌደራል የሥነ ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር ዶ/ር ሳሙኤል ኡርቃቶ የመድረኩ ዋና ዓላማ ሲገልፁ፣ መረጃውን በማጥራት ለአለም ባንክ ሪፖርት ለመላክና በቀጣይ ተግባሩ ከሚመለከታቸው ባለድረሻ አካላት ጋር ውይይት ለማድረግና ትኩረት የሚደረጉ ተግባራት የሚለይበት እንደሆነ ጠቁመዋል፡፡

ኮሚሽነሩ አክለውም ከአለም ባንክ ጋር ባደረገው ስምምነት መነሻነት ሰባቱ ፕሮጀክቶች (UIIDP, ESPES, CALM, EOP, ELEAP, GEQIP and HSDG) የተከናወኑ ተግባራትን ከሙስናና ብልሹ አሰራር ነፃ መሆናቸውን በማረጋገጥ ሪፖርት የሚደረግ መሆኑን የገለፁ ሲሆን፤ ልማቱ ምን ያክል የተሳካ እንደሆነ መረጋገጥ እንዳለበት አመላክተዋል፡፡

በቀጣይ ሪፖርቱን መነሻ በማድረግ የኮሚሽኑ የስራ መሪዎች ስልጠና የመስጠት፣ መረጃ የማመንጨት፣ የአሰራር ስርዓት ጥናት የማካሄድ እና ግንዛቤ የመፍጠር ስራን እንዲያከናውኑ አሳስበዋል፡፡








የማጣራት ስራው የተከናወነው ከትግራይ ክልል በስተቀር በሌሎች የከተማ አስተዳደር እና የክልል ከተማና ወረዳዎች በኮሚሽኑ 84 አመራርና ሰራተኞች ሲሆን ፕሮጀክቱ በ147 ከተሞች ላይ ተግባራዊ መሆኑን መረዳት ተችሏል፡፡


ከ30 ሚሊየን ብር በላይ ገንዘብ ለግል ጥቅማቸው አውለዋል በተባሉ አራት የብሄራዊ መረጃ እና ደህንነት አገልግሎት ሰራተኞች ላይ የምስክር ቃል ተሰማ

ገጽ 2



“የተገኘው የፈተና ውጤት ከስርቆትና ከኩረጃ በፀዳ መልኩ በትክክል የተመዘገበ መሆኑን ያመላከተ ነው”

ገጽ 4

በደቡብ ክልል በሙስና የተጠረጠሩ 49 ግለሰቦች ላይ ክስ ለመመስረት ዝግጅት ተጠናቋል

ገጽ 4

ለፌዴራል ተቋማት የግዥ የሥራ ኃላፊዎች በመንግስት ግዥ ላይ የሚስተዋሉ የሙስና ስጋቶችና መከላከያ ስልቶች ላይ የዓቅም ግንባታ ስልጠና ተሰጠ

ገጽ 5


## የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ህዝቦች ክልል አመራር በአንድነት ቆሞ ሌብነትና ብልሹ አሠራርን በጽናት ይታገላል

የክልሉ አመራር በአንድነት ቆሞ ሌብነትና ብልሹ አሠራርን በጽናት መታገል እንዳለበት የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ህዝቦች ክልል የመንግስት ዋና ተጠሪ አቶ ፀጋዬ ማሞ ተናገሩ።

አመራሩ የጠራ የአስተሳሰብና የተግባር አንድነት በመያዝ የተጀመረውን የብልጽግና ጉዞ ለማሳካት ጥረት ማድረግ የሚያስችል ምክክር ከክልሉ ከፍተኛና መካከለኛ አመራሮች ጋር ተደርጓል።

የመድረኩን መጠናቀቅ ተከትሎ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ህዝቦች ክልል የመንግስት ዋና ተጠሪ አቶ ፀጋዬ ማሞ በሰጡት መግለጫ “አመራሩ የተደራጀ ስርቆትንና ብልሹ አሠራርን እንዲሁም ጽንፈኝነትን በጽናት ሊታገል ይገባል”።

እንደ ሀገር በተጀመሩ የሰላም፣ የልማትና ሌሎች ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ አመራሩ የጋራ ግንዛቤና የተግባር አንድነት እንዲይዝ ለማስቻል ውይይት መደረጉንም ተናግረዋል።

የፌዴራል መንግስት ከህወሃት ጋር ያደረገውን የሰላም ስምምነት ተከትሎ ለሚያደርጋቸው የተግባራዊነት እንቅስቃሴዎች የክልሉ አመራሮች የሚጠበቅባቸውን ድጋፍ ለማድረግ ከመግባባት ላይ መደረሱን ጠቅሰዋል።

“ሌብነት፣ ብልሹ አሰራርና ጽንፈኝነት የህዝብ ጠላት ናቸው” ያሉት አቶ ፀጋዬ፤ ይህ ብልሹ አሰራር ማንንም የማይወግንና የልማት ጸር መሆኑን አመራሩ ተረድቶ በአንድነት ይታገላል ብለዋል።

የተደራጀ ስርቆትንና ብልሹ አሠራርን ለመታገል ክልሉ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ውስጥ መግባቱን ገልጸው




በተለይም ሀሰተኛ የትምህርት ማስረጃ የማጥራት ስራ በቁርጠኝነት እየተሰራ መሆኑን ለአብነት አንስተዋል።

በክልሉ እስካሁን በተደረገ ሐሰተኛ የትምህርት ማስረጃ የማጥራት ሥራ 1 ሺህ 870 የባለሙያ እንዲሁም 170 የአመራር የትምህርት መረጃ ሐሰተኛ ሆኖ መገኙትን ጠቁመዋል።

በሀሰተኛ የትምህርት ማስረጃ ሊባክን የነበረ ከ50 እስከ 60 ሚሊዮን ብር የሚገመት የመንግስት ሀብት ማዳን እንደተቻለም አቶ ጺጋዬ በመግለጫቸው አንስተዋል።

የክልሉ ከፍተኛ አመራር ክልላዊ እና ሃገራዊ ጉዳዮች ላይ ለሁለት ቀናት ባደረገው ሰፊ ውይይት በቀጣይ ሊከናወኑ በሚገባቸው ሁለንተናዊ እንቅስቃሴዎች ላይ በትኩረት መስራት የሚያስችል የጋራ መግባባት ላይ በመድረስ መጠናቀቁን ማመላከታቸውን ከኢዜአ የተገኘው መረጃ ይጠቁማል።

# ኮሚሽኑ የሀብትና የገቢ ምንጭ ትክክለኛነትን የማረጋጥ ተግባር አስፈላጊነትን ከመረጃ ሰጪ ተቋማት ተወካዮች ጋር የስራ ማስጀመሪያ ስልጠናዊ ውይይት አካሄደ

የሀብትና የገቢ ምንጭ ትክክለኛነት ማረጋጥ ተግባር ላይ የጋራ ግንዛቤ ለመፍጠር ከባንኮች፣ በክፍለ ከተማ ከሚገኙ የይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ እና መሬት ልማት አስተዳደር፣ አሽከርካሪና ተሽከርካሪ፣ ሪል እስቴት እና ከኢንሹራሶች እንዲሁም ፍቃድ ሰጭ ተቋማት ከተወጣጡ ከ80 በላይ ተሳታፊዎች በተገኙበት በአዲስ አበባ ኢንተር ሌግዠሪ ሆቴል ስልጠናዊ ውይይት አካሄደ፡፡





የመክፈቻ ንግግር ያደረጉት የፌዴራል የስነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የጥቅም ግጭት መከላከልና ማስወገድ ስራ አስፈፃሚ አቶ መስፍን በላይነህ መድረኩ የሀብትና የገቢ ምንጭ ትክክለኛነት ማረጋጥ ተግባር ላይ የጋራ ግንዛቤ በመያዝ፣ በፌደራል የሥነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን እና በመረጃ ሰጪ ተቋማት መካከል ፈጣን፣ ተዓማኒነት ያለው እና ሚስጥራዊነቱ የተጠበቀ የመረጃ ልውውጥ እንዲኖር ማድረግ አስፈላጊ እንደሆነ አመላክተዋል።



መድረኩ የሀብት ምንነት፣ የሀብት ማፍራት መብት፣ የሀብት ምዝገባ ሥርዓት በኢትዮጵያ እና ጠቀሜታው ላይ የጥቅም ግጭት ምንነት፣ ማሳወቅ እና ማስወገድ ላይ እና በሀብት ምንጭ ትክክለኛነት ማጣራት ስራ የሚሰበሰቡ የመረጃ አይነቶች እንዲሁም ምንጩ ያልታወቀ ሀብት ማፍራት በኢትዮጵያ ህግ፣ ተግዳሮቶች እና ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች ላይ ያተኮረ መሆኑን ገልፀዋል።

ከኮሚሽኑ እና ከመረጃ ሰጪ ተቋማት ምን ይጠበቃል በሚሉ ሃሳቦች ዙሪያ የተሻለ ግንዛቤ በመያዝ እና በፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የሀብት ምንጭ ማጣራት የመረጃ አሰባሰብ ረቂቅ ፕሮቶኮል ላይ ግብዓት በማሳባሰብ፤ በቀጣይ በኮሚሽኑ እና በመረጃ ሰጪ ተቋማት መካከል በቴክኖሎጂ የታገዘ፣ ቀልጣፋ እና ሚስጢራዊነቱን የተጠበቀ መረጃ ልውውጥ እንዲኖር ለማድረግ ትልቅ ፋይዳ እንዲኖር የመነሻ ሰነድ ለተሳታፊዎች የቀረበ ሲሆን፤ ሰነዱን መነሻ በማድረግ ተሳታፊዎች ሀሳብ፣ አስተያየት በማቅረብ የጋራ ግንዛቤ መያዝ ተችሏል።



ለኮሚሽኑ በተሻሻለው የማቋቋሚያ አዋጁ 1236/2013 እና በአዋጅ ቁ 668/2002 መሠረት የተሿሚዎች፣ የተመራጮችና ምዝገባው የሚመለከታቸውን የመንግሥት ተቋማት እና ህዝባዊ ድርጅቶች ሠራተኞችን ሀብት የመመዝገብ፣ መረጃ ተደራሽ የማድረግ፣ የመረጃ ትክክለኛት የማረጋገጥ እና የጥቅም ግጭትን የመከላከል ሥልጣንና ኃላፊት መሰጠቱ ይታወቃል።

# ከ30 ሚሊየን ብር በላይ ገንዘብ ለግል ጥቅማቸው አውለዋል በተባሉ አራት የብሄራዊ መረጃ እና ደህንነት አገልግሎት ሰራተኞች ላይ የምስክር ቃል ተሰማ

ከሲሚንቶ ግዢ ጋር ተያይዞ ከ30 ሚሊየን ብር በላይ ገንዘብ ያለአግባብ ለግል ጥቅም አውለዋል ተብለው በተከሰሱ አራት የብሄራዊ መረጃ እና ደህንነት አገልግሎት ሰራተኞች ላይ የምስክር ቃል ተሰማ።

የምስክሮችን ቃል ያደመጠው የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ልደታ ምድብ 3ኛ የሙስና ጉዳዮች ወንጀል ችሎት ዐቃቤ ህግ ያቀረባቸውን የምስክሮችን ቃል መርምሮ ብይን ለመስጠት ተለዋጭ ቀጠሮ ሰጥቷል።

የምስክር ቃል የተሰማባቸው ተከሳሾች የብሄራዊ መረጃ እና ደህንነት አገልግሎት ተቋም የኮንስትራክሽን እና ሎጂስቲክስ ምክትል ዳይሬክተር አቶ ተስፋዬ ደሜ፣ በተቋሙ የኮንስትራክሽን እና ሎጂስቲክስ ግዢ ዋና ክፍል ኃላፊ አቶ አሸናፊ ተስፋዬ፣ በተቋሙ የግዢ ባለሙያ ናቸው የተባሉ ቱጅባ ቀልቤሳ እና 4ኛ ተከሳሽ ሙስጠፋ ሙሳ ናቸው።

ተከሳሾቹ የብሄራዊ መረጃ እና ደህንነት አገልግሎት ተቋም የግዢ ፍላጎት ሳይኖረው ትዕዛዝ ባልተሰጠበት እና ከተቋሙ ዕውቅና ውጪ የግዢ ባለሙያ ሆነው ሲሰሩ፥ ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ለማግኘት በማሰብ በ2013 እና 2014 ዓ.ም በተለያዩ ቀናቶች ለተቋሙ ነው በሚል ከሁለት ፋብሪካዎች የገዙትን 29 ሺህ 200 ኩንታል ሲሚንቶ ምርት በተለያዩ ቀናቶች ለግለሰቦች በመሸጥ ከ30 ሚሊየን ብር በላይ ለግል ጥቅማቸው አውለዋል ሲል ዐቃቤ ህግ ታህሳስ 3 ቀን 2015 ዓ.ም በዋለው ችሎት በዋና ወንጀል አድራጊነት ተካፋይ በመሆን ስልጣንን አላግባብ መገልገል ከባድ የሙስና ወንጀል ክስ መመስረቱ ይታወሳል።

ተከሳሾቹ ክሱ ከደረሳቸውና በንባብ ከተሰማ በኋላ ወንጀሉን አልፈጸምንም ሲሉ የሰጡትን የዕምነት ክህደት ቃል ተከትሎ ዐቃቤ ህግ ለወንጀሉ መፈጸም ያስረዱልኛል ያላቸውን 3 ምስክሮችን አሰምቷል፡፡

የምስክሮችን ቃል ያዳመጠው ችሎቱ የምስክር ቃል መርምሮ ብይን ለመስጠት ለየካቲት 22 ቀን 2015 ዓ.ም ተለዋጭ ቀጠሮ መሰጠቱን ከፋና ብርድካስት ኮርፖሬት ድረ-ገፅ የተገኘው መረጃ ያመላክታል።

ብሔራዊ የሙስና ድርጊቶች ጥቆማ መስጫ አድራሻዎች
ስልክ፦ 9555
አጭር የፅሁፍ መልዕክት፦ 9555
ድረ ገፅ፦ http://www.9555pmo.et/
ኢሜይል፦ http://9555pmo.et/
ቴሌግራም፦https://t.me/PMOfeedback

የሙስናና ብልሹ አሰራር ድርጊቶችን በጥቆማ መስጫ አድራሻዎች ያጋልጡ፣ይጠቁሙ!!

ከሙስና የጸዳች ኢትዮጵያ
CORRUPTION FREE ETHIOPIA

# ፀረ-ሙስና

## በፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የሚዘጋጅ ወርሃዊ ጋዜጣ


ስልክ 011552-77-79
ፖ.ሳ.ቁ 34799
ኢ-ሜይል FeaccEthiopia2013@et
ድረ-ገጽ www.feacc.gov.et
ፌስቡክ www.facebook.com/feaccOfficial
ቴሌግራም t.me/feacc
ትዊተር www.twitter.com/EthiopiaFeacc
ዩቲዩብ Federal Ethics & Anti-Corruption Commission

**ለሀብት ማሳወቅና ምዝገባ ስራዎች**
**www.feaccdars.gov.et**


## ለፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የሙስና ወንጀል ጥቆማ መስጫ አድራሻዎች


ስልክ 011552-77-92/ 011553-38-52
ሞባይል 0935947533
ፖ.ሳ.ቁ 34799
ድረ-ገጽ www.feacc.gov.et
ኢ-ሜይል CorruptionReportEthiopia@feacc.gov.et
ቴሌግራም t.me/CorruptionPointing
ዋትስአፕ wa.me/qr/5IGXTSIYUMPBF1


# ርዕሰ -አንቀፅ

## ምንጩ ያልታወቀ ሀብትን ማጋለጥ ሙስናን ለመከላከል ላቅ ያለ ሚና አለው!!!

የዓለም እና አህጉር አቀፍ ኮንቬንሽኖች፡- የተባበሩት መንግስታት የፀረሙስና ስምምነት (UNCAC)እና የአፍሪካ ኅብረት የሙስና መዋጊያና መከላከል ስምምነት (AUCPCC) እንዲሁም የኢንተር አሜሪካን ኮንቬንሽን ፀረ-ሙስና ስምምነት (IACAC)) አባል ሀገራት ምንጩ ያልታወቀ ሀብትን የሙስና ወንጀል አድርገው ህግ እንዲደነግጉ ያነሳሳቸው ምክንያት ለምን ይሆን? ብለው ከጠየቁ ወደምንጩ ያልታወቀ ሀብት ትርጉም እናመራለን፡፡ ምንጩ ያልታወቀ ሀብት ማለት ሊገለፅ የማይችል ሀብት መያዝ ወይም ከገቢ በላይ ሀብት መያዝ ሲሆን በወንጀልም ያስጠይቃል፤ ያስቀጣልም፡፡

ታዲያ ይህ የሀገርና የእድገት ነቀርሳ የሆነን ድርጊት ከምንጩ ለማድረቅ እና ለማጋለጥ የሚረዱ መነሻ ሁኔታዎች የሀብት ምዝገባና ማሳወቅ ስርዓት፣ የአኗኗር ዘይቤዎች ፍተሻ፣ አጠራጣሪ የፋይናንስ ዝውውሮች እና ሌሎች ምርመራዎች ምንጩ ያልታወቀ ሀብት እንደተፈጸመና እንዳልተፈፀመ የሚጠቁም መረጃዎች መሆናቸውን ግንዛቤ መያዝ ያስፈልጋል። ይህ ከሆነ ትክክለኛና ግልፅ ሀብት የማፍራት መብት እንደሚነለብት አያጠያይቅም፡፡

በነገራችን ላይ የሀብትና የንብረት መብት ከጥንት ጀምሮ የህግ ጥበቃ ተሰጥቶት እንደየስርዓተ ማህበሩ ለዚያ የሚመጥን አሰራርና አደረጃጀት ተዘርግቶለት ከጊዜ ወደ ጊዜ ከሰው ልጆች የእውቀትና መስተጋብራዊ አድማስ መስፋት ጋር እያደገ የመጣ መሰረታዊ የሰው ልጆች መብት ነው፡፡ ይህ መብት አሁን ባለንበት ዘመን ሳይቀር ከፍተኛ ግምት ተሰጥቶት አገሮች በህገ መንግስታቸውና ከዚያ በታች ዝርዝር ባሉ ሌሎች ህጐች እንደ አንድ የዜጐቻቸው የሰብዓዊ መብትና ነፃነት ማረጋገጫ ወስደው በተግባር እየሰሩበት ይገኛሉ፡፡

በ1948 እ.አ.አ የወጣው ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ድንጋጌ አንቀጽ 17 ሁሉም ሰው በግል ወይም በጋራ ንብረት የማፍራት፣ የንብረት ባለቤት የመሆን እና ያለፍርድ ንብረቱን ሊነጠቅ እንደማይችል ይደነግጋል፡፡

በተያያዘም ሀብት ማሳወቅና ምዝገባ ስርዓት ተቋማዊ አሠራርን በግልፅነትና በተጠያቂነት ለመመስረት፣ ሙስናና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል፣ መልካም አስተዳደርን በማስፈን የጥቅም ግጭት ለመከላከልና ለማስወገድ ያግዛል፡፡

በተለይም የመንግስት ባለሥልጣናት፣ ተመራጮች፣ ተሿሚዎች እና ሠራተኞች ሀብት እና የጥቅም ምንጫቸው በህዝብ ዘንድ እንዲታወቅ የሚደረግበት ዋናው ምክንያት ያላቸው ሃብት እና ንብረት የመንግሥት ሥልጣን እና ኃላፊነታቸውን አላግባብ በመጠቀም ያፈሩት መሆን አለመሆኑን ለመለየት እና የጥቅም ግጭትን ለማስወገድ የሚያግዝ የግልፅነት እና የተጠያቂነት አሰራር ማራመጃ ስርዓት ነው፡፡ ይህ አሰራርም ምንጩ ያልታወቀ ሀብት ባለቤት ሆኖ በሙስና ወንጀል ከመዘፈቅ ያድናል፡፡

ሀገራችን ኢትዮጵያ ምንጩ ያልታወቀን ሀብት የወንጀል አካል አድርጋ የደነገገችው በ1996 ዓ.ም በወጣው የተሻሻለው የወንጀል ህግ ነው፡፡ በተባበሩት መንግስታት ፀረ-ሙስና ኮንቬንሽን አንቀፅ 20 እና በአፍሪካ ሕብረት የሙስና መከላከያና መዋጊያ ኮንቬንሽን አንቀፅ 8 መሰረት አባል ሀገራት አላግባብ መበልፀግን የሙስና ወንጀል አድርገው መደንገግ እንዳለባቸው የሚደነግግ ሲሆን፣ በዚሁ መሰረት ኢትዮጵያ እነዚህን ኮንቬንሽኖች በአዋጅ ቁጥር 544/1999 እና 545/1999 የሀገሪቱ የሕግ አካል አድርጋ በፓርላማ አፅድቃለች፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ኢትዮጵያ በኮንቬንሽኑ የገባቸው የሙስና ወንጀሎችን ለመደንገግ በወጣው አዋጅ ቁጥር 881/2015 አንቀጽ 21 ምንጩ ያልታወቀ ሀብትን የሙስና ወንጀል በማድረግ የደነገገ ሲሆን፣ ድንጋጌውም በመንግሥትና በግሉ ዘርፍ የሚስተዋሉ ብልሹ አሰራሮችን ለመዋጋትና ለመከላከል የሚረዳ ነው።

በሀገራችን ምንጩ ያልታወቀ ሀብት የማጋለጥ እና የተመዘበረ ሀብትን የማስመለስ ተግባር የጋራ ትብብር እና ቅንጅታዊ አሰራርን የሚሻ መሆኑ አያጠያይቅም፡፡ በጋራ ትብብር ተግባርም፥ የሲቪል ማህበረሰብ አባላት፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ የመንግስት ተቋማት ወይም ህዝባዊ ድርጅቶች የፀረ-ሙስና ተወካዮችን፣ የመገናኛ ብዙኃን እና ሌሎች አካላት ላቅ ያላ ሚና አላቸው፡፡

በተለይም ደግሞ ምንጩ ያልታወቀ ሀብት ጉዳይ ላይ የተሳካ ክስ ለመመስረት የሀብት ምዝገባና መረጃ ትክክለኛነት ማረጋገጥ በሚያከናውኑ የፀረ-ሙስና ተቋማት፣ በፋይናንስ ደህንነት ማዕከል፣ የግብር ባለስልጣን እና ከቋሚ ንብረት ምዝገባ ተቋም እንዲሁም ሌሎች ዓለም ዓቀፍ ተቋማት ጋር ትስስር መፍጠር ይጠይቃል፡፡ ምንጩ ያልታወቀ ሀብትን ከመመርመርና ከመክሰስ አኳያ ዋናው ተግዳሮት የመረጃ አሰባሰብ ጉዳይ ነው፡፡

በተመሳሳይ በሀገር ደረጃ በቴክኖሎጅ የታገዘ የመረጃ ቋት አለመዘርጋቱ፣ ምንጩ ያልታወቀ ሀብት ማጋለጥ እና ህጋዊ እርምጃ በሚወስዱ አካላት መካከል ያለው ቅንጅት ዝቅተኛ መሆን፣ ምንጩ ያልታወቀ ሀብትን የሚያጋልጡ ዜጎች/ጠቋሚዎች ቁጥር እጅግ አነስተኛ መሆን፣ ለጠቋሚዎች የሚሰጥ ከለላ ወቅታዊ አለመሆን፣ ለጠቋሚዎች የሚሰጥ ማበረታቻ ተግባራዊ አለመሆን ምንጩ ያልታወቀ ሀብትን ለማጋለጥ ቁልፍ ተግዳሮቶች ናቸው፡፡

በአጠቃላይ ተግዳሮቶችን ለመቅረፍ ምንጩ ያልታወቀ ሀብትን የማጋለጥ ሚናን በስኬት ለመወጣት በቀጣይ የተጀመሩ የኦንላይን የሀብት ምዝገባ ተግባር በጥራትና በፍጥነት አጠናክሮ ማስቀጠል፤ የዘርፍ ተኮር የሀብት መረጃ ትክክለኛነት በማረጋገጥ ወቅታዊ ምዝገባ ማካሄድ፣ የመረጃ ትክክለኛነት ማረጋጋጥ፣ አላግባብ መበልፀግ እና የጥቅም ግጭትን ማጋለጥ በሚያስችል ሁኔታ አጠናክሮ በመተግበር የገቢ ምንጭን ማስመዝገብ ያስፈልጋል፡፡

በተጨማሪም አላግባብ ለመበልፀግ በሚሞክሩ አካላት ላይ አስተማሪ የሆነ የህግ ቅጣት እንዲጣል በኮሚሽኑ እና በፍትህ አካላት መካከል የበሰለና የተጠናከረ ትብብር መፍጠር ተግዳሮቶቹን የበለጠ ይቀንሳል፡፡ እንደ (Transparancy international, 2015) መረጃ በዜጎች፣ በመንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች እና በጋዜጠኞች የሚመጡ ጥቆማዎችም ሙስና እና ብልሹ አሠራርን በተለይ ከፍተኛ ምንጩ ያልታወቀ ሀብትን የማጋለጥ ሚናቸው ወደር የለሽ ነው፡፡

ዜጎች መረጃና ማስረጃን መሰረት በማድረግ ምንጩ ያልታወቀ ሀብትን የሚያጋልጡና የሚጠቁሙ ከሆነ በሀብት ማሳወቅና ምዝገባ አዋጅ 668/2002 የተደነገገውን 25 በመቶ (ከሚወረስ ሀብት) ማበረታቻ ተጠቃሚ ይሆናሉ፡፡ ምንጩ ያልታወቀ ሀብትን በማጋለጣቸው በራሳቸው እና በቤተሰቦቻቸው ላይ ጉዳት እንዳይደርስባቸው የሚያደርግ ግልፅ ሥርዓት በመዘርጋት እና ፈጣን ከለላ እና ጥበቃ በማድረግ ሙስናን መከላከል አስፈላጊ ነው፡፡

ስለሆነም ተገቢውን ከለላ እና ጥበቃ በማድረግ፣ ተገቢ የምርመራ እና የክስ ስርዓትን በታላቅ ኃላፊነት በመምራት ምንጩ ያልታወቀ ሀብትን በጋራ በማጋለጥ ሙስናን ልንከላከል ይገባል፡፡



# “የተገኘው የፈተና ውጤት ከስርቆትና ከኩረጃ በፀዳ መልኩ በትክክል የተመዘገበ መሆኑን ያመላከተ ነው”

### ፕሮፌሰር ብርሃኑ ነጋ

የትምህርት ሚኒስትሩ ፕሮፌሰር ብርሃኑ ነጋ በ2014 ዓ.ም የ12ኛ ክፍል ፈተና የተገኘው የፈተና ውጤት ከስርቆትና ከኩረጃ በፀዳ መልኩ በትክክል የተመዘገበ መሆኑን የሚያመላክት እንደሆነ ገልጸዋል።

የዚህ አመት የፈተና ውጤት አንድምታም ለዓመታት ሲንከባለል የቆየ በርካታ ችግሮች መገለጫ እና ተሸፋፍኖ የቆየውን እውነተኛ የትምህርት ስርዓታችን ያለበትን ደረጃ የሚያሳይ መሆኑንም ተናግረዋል፡፡

ሚኒስትሩ በመግለጫቸው በዩኒቨርስቲዎች ውስጥ የተሰጠው ፈተና ስርቆትን እና ኩረጃን ማስቀረት የተቻለበት እንደሆነ ገልፀው ውጤቱም የዚህ ማሳያ ነው ብለዋል።

በ2014 ዓ.ም በተሰጠው ፈተና በሁለቱም የትምህርት መስክ ፈተናውን ከወሰዱት 896 ሺህ 520 ተማሪዎች ውስጥ 29 ሺህ 909 የሚሆኑት ተማሪዎች 50% እና ከዚያ በላይ ማስመዝገባቸው ገልፀው፤ በተገኘው ውጤት መሰረትም ከ50 በመቶ በታች ያመጣ ተማሪ ወደ ዩኒቨርስቲ እንደማይገባም ተናግረዋል።

በመሆኑም በቀጣይ እንደሀገር በትምህርቱ ዘርፍ የተሻለ ውጤት ለማስመዝገብ የሁሉም አካላት ቅንጅት እንደሚፈልግ ሚኒስቴሩ መግለፃቸውን በትምህርት ሚኒስትር የማህበራዊ ድረ-ገፅ የተገኘው መረጃ ያመላክታል።

# በደቡብ ክልል በሙስና የተጠረጠሩ 49 ግለሰቦች ላይ ክስ ለመመስረት ዝግጅት ተጠናቋል

በደቡብ ክልል በተለያዩ ዘርፎች በሙስና የተጠረጠሩ 49 ግለሰቦች ላይ ክስ ለመመስረት ዝግጅት ማጠናቀቁን የክልሉ ጸረ ሙስና ኮሚቴ አስታውቋል፡፡

የደቡብ ክልል ሰላምና የጸጥታ ቢሮ ሃላፊ እንዲሁም የፀረ ሙስና ኮሚቴ ሰብሳቢ አቶ አለማየሁ ባውዲ፥ ኮሚቴው ሙስና የሚስተዋልባቸውን ወሳኝ ዘርፎች በመለየት እና እቅድ በማዘጋጀት ወደ ስራ መግባቱን አንስተዋል፡፡

በእቅዱ ከዚህ በፊት በከባድ ሙስና ተጠርጥረው የነበሩ እና በተለያዩ ምክንያቶች ተደናቅፈው ለቀሩ ጉዳዮች ቅድሚያ መሰጠቱን ጠቁመዋል፡፡

ከዚህ ባለፈም በክልሉ በሁሉም አካባቢዎች ከተቋማት እና ግለሰቦች አዳዲስ የሙስና ጥቆማዎችን የመቀበል እና የማደራጀት ስራ መሰራቱን ነው የገለጹት።

እስካሁን በተከናወነ የማጣራት ስራም በአራት መዝገቦች በሙስና የተጠረጠሩ 49 ግለሰቦች ላይ ክስ ለመመስረት ዝግጅት መጠናቀቁን ተናግረዋል፡፡

በሙስና ወንጀል የተጠረጠሩ ግለሰቦች በሙሉ እንዲያዙና እና ያላቸው ቋሚ እና ተንቀሳቃሽ ሃብትም መታገዱን አስረድተዋል።

ግለሰቦች ከመሬት ምዝበራ፣ ከአፈር ማዳበሪያ፣ ከአገልግሎት አሰጣጥ እና ሌሎች ጉዳዮች ጋር በተገናኘ በሙስና ወንጀል መጠርጠራቸውን ሰብሳቢው ገልጸዋል፡፡

አሁን ላይ ከተቋማት እና ግለሰቦች በርካታ ጥቆማዎች እየቀረቡ መሆኑን የገለጹት አቶ አለማየሁ፥ ጥቆማዎችን የመለየት ስራ እየተከናወነ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

የቀረቡ መረጃዎችን ወደ ማስረጃ ለመቀየር እና አስፈላጊውን ማጣራት ለማድረግ ንዑስ ኮሚቴ ተዋቅሮ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት እየተሰራ ነው ብለዋል።

ሙስና ለሀገር እድገት እና ለፍትሃዊ ተጠቃሚነት እንቅፋት ነው ያሉት ሰብሳቢው፥ ማህበረሰቡ ጥቆማ ከማድረግ ባለፈ አስፈላጊውን እገዛ እንዲያደርግ ጥሪ መቅረቡን ፋና ብሮድካስት ኮርፖሬት ዘግቧል፡፡

# የሀብት ምዝገባ ስርዓት ምንጩ ያልታወቀ ሀብትን ለማጋለጥ ባለው ፋይዳ ላይ ውይይት ተካሄደ









የሀብት ምዝገባ ስርዓት ምንጩ ያልታወቀ ሀብትን ለማጋለጥ ባለው ፋይዳ ላይ የህዝብ ተወካዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢዎች፣ የፌደራል ተቋማት ሃላፊዎች፣ የአፋር ክልል የስራ ሃላፊዎች፣ የከተማ አስተዳደርና የክልል የስነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽነሮች እንዲሁም የተለያዩ ባለድርሻ አካላት በተገኙበት በአፋር ክልል ውይይት ተካሄዷል።

የአፋር ክልል ርዕሰ መስተዳደር ተወካይና ጽ/ቤት ምክትል ኃላፊ በመክፈቻ ንግግራቸው በክልሉ የፀረሙስና ኮሚቴ በማቋቋም የተጀመረውን የሙስና ትግል አጠናክሮ ለመቀጠል እየተሰራ እንደሚገኝ ገልፀዋል።

የኮሚሽኑ የሀብት ምዝገባና የጥቅም ግጭት ማስወገድ መሪ ስራ አስፈፃሚ አቶ መስፍን በላይነህ የመወያያ ሀሳቡ ሲቀርብ ምንጩ ያልታወቀ ሀብት ማጋለጥ ከፌደራል ፓሊስ፣ ከፍርድ ቤትና ከፍትህ አካላት በጋራ መስራት እንደሚያስፈልግ ገልፀው፤ ምንጩ ያልታወቀ ሀብትን ለማጋለጥ በቴክኖሎጂ መታገዝ እንዳለበት፣ ለጠቋሚዎች ስለሚሰጥ ከለላ እንዲሁም ለጠቋሚዎች የሚሰጠው 25% ማበረታቻ በተመለከተ ገለፃ አድርገዋል።

ተሳታፊዎች የቀረበውን የመነሻ ሰነድ መሰረት በማድረግ ሙስናን ለማጋለጥ ትኩረት የሚሰጣቸውን ሀሳቦችን በማንሳት የጋራ ውይይት ማድረግ ችለዋል።

የማጠቃለያ ንግግር ያደረጉት የፌደራል የስነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር ዶ/ር ሳሙኤል ኡርቃቶ በሀገራችን ምንጩ ያልታወቀ ሀብት የማጋለጥ እና የተመዘበረ ሀብትን የማስመለስ ተግባር የጋራ ትብብር እና ቅንጅታዊ አሰራርን የሚሻ መሆኑን አመላክተዋል። በጋራ ትብብር ተግባርም፥ የሲቪል ማህበረሰብ አባላት፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ የመንግስት ተቋማት ወይም ህዝባዊ ድርጅቶች የፀረ-ሙስና ተወካዮችን፣ የመገናኛ ብዙኃን እና ሌሎች አካላት ላቅ ያላ ሚና እንዳላቸው ጠቁመዋል።

አላግባብ ለመበልፀግ በሚሞክሩ አካላት ላይ አስተማሪ የሆነ የህግ ቅጣት እንዲጣል በኮሚሽኑ እና በፍትህ አካላት መካከል የበሰለና የተጠናከረ ትብብር በመፍጠር ሙሰኞችን ተጠያቂ የማድረግ ስራ እንደሚከወን ገልፀዋል።

# በሶማሌ ክልል ለሙስና በር የሚከፍቱ አሰራሮችን ለይቶ ለማስተካከል እየተሰራ ነው

በሶማሌ ክልል ለህዝብ አገልግሎት በሚሰጡ ተቋማት የሚስተዋሉ ብልሹና ለሙስና በር የሚከፍቱ አሰራሮችን ለይቶ ለማስተካከል ግብረ-ሃይል ተቋቁሞ ስራ መጀመሩን ተገለጸ።

የክልሉ መንግስት በቅርቡ በኤረር ዞን ፊቅ ከተማ ያካሄደውን የስራ ገምገማና ውሳኔ ላይ የተደረሰባቸውን ጉዳዮች አስመልክቶ ጋዜጣዊ መግለጫ ተሰጥቷል።

መግለጫውን በጋራ የሰጡት የክልሉ ርዕሰ መስተዳድር ጽህፈት ቤት ኃላፊ ዶክተር ሁሴን ሃሺና የብልፅግና ፓርቲ የሶማሌ ክልል ጽህፈት ቤት ኃላፊ ኢንጂነር መሀመድ ሻሊ ናቸው።



ዶክተር ሁሴን እንዳመለከቱት፤ በግምገማ መድረኩ ላይ በየደረጃው የሚገኙ መንግስታዊ ተቋማት ለህዝብ የሚሰጡት አገልግሎት በጥልቀት እንዲፈተሽ አቅጣጫ ተቀምጧል።

በተቋማቱ የሚስተዋሉ ብልሹና ለሙስና በር የሚከፍቱ አሰራሮችን ለይቶ ለማስተካከል ግብረ-ሃልይ ተቋቁሞ ስራ ተጀምሯል ነው ያሉት።

ይህም ቀደም ብሎ የተጀመረው የሌብነትና ብልሹ አሰራርን የመከላከሉ አካል መሆኑን የገለጹት ዶክተር ሁሴን፤ በክልሉ የተቋቋመው የፀረ ሙስና ኮሚሽንና የህዝብ ቅሬታ ሰሚ ኮሚሽን የሚሰጠው ድጋፍ ተጠናክሮ እንደሚቀጥል አስታውቀዋል።


የብልፅግና ፓርቲ የሶማሌ ክልል ጽህፈት ቤት ኃላፊ ኢንጂነር መሀመድ ሻሊ በበኩላቸው፤ በግምገማ መድረኩ ባለፉት አራት ዓመታት በክልሉ በሰላም፣ በህግ የበላይነት፣ በመንግስታዊ አደረጃጀት ዙሪያ የተመዘገቡ ስኬቶችና ቀጣይ አቅጣጫዎች ዙሪያ ውይይት መካሄዱን ተናግረዋል።

በዚህም ክልሉ ከአጎራባች ክልሎች ጋር ይስተዋሉ የነበሩ ያለመግባባቶች ሙሉ ለሙሉ በመፍታት የሚያኮራ ስራ እንደተከናወነ መግባባት ላይ መደረሱን ጠቅሰዋል።

ልማትና በሰብዓዊ መብት ጉዳዮች እንዲሁም የክልሉ አመራር አካላት የአመለካከትና የተግባር አንድነት እንዲፈጥሩ በርካታ የአቅም ግንባታ ስራዎች መከናወናቸውን አስረድተዋል ሲል የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት ድርጅት ዘግቧል።

# ለፌዴራል ተቋማት የግዥ የሥራ ኃላፊዎች በመንግስት ግዥ ላይ የሚስተዋሉ የሙስና ስጋቶችና መከላከያ ስልቶች ላይ የዓቅም ግንባታ ስልጠና ተሰጠ

በፌደራል ተቋማት በግዥ ለሚሰሩ የግዥ የስራ ኃላፊዎች በመንግስት ግዥ ላይ የሚስተዋሉ የሙስና ስጋቶችና መከላከያ ስልቶች የዓቅም ግንባታ ስልጠና በሀዋሳ ሳውዝ ስታር ሆቴል ለሶስት ተከታታይ ቀናት ተሰጠ፡፡









የመክፈቻ ንግግር ያደረጉት የፌዴራል የስነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ም/ኮሚሽነር አቶ ወዶ አጦ የእንኳን ደህና መጣችሁ መልዕክት ሲያስተላልፉ ስልጠናው ወቅታዊ መሆኑና የፌደራል ተቋማት፣ የዩኒቨርስቲ እና የልማት ድርጅቶች የግዥ ኃላፊዎች በተቋማቸው የሚስተዋሉ የሙስናና ብልሹ አሰራሮች በተጨባጭ ሁኔታ ምን እንደሚመስል ግንዛቤ የሚገኝበት መሆኑን አመላክተዋል።

ሙስና በሀገራችን እጅግ አሳሳቢና ለዜጎች ማህበራዊ ቀውስ ማነቆ በመሆን ሙስና ከኑሮ ውድነትና ከስራ አጥነት ቀጥሎ በሶስተኛ ደረጃ መቀመጡን ጥናቶች እንደሚያመለክቱ ገልፀው፣ ሁላችንም የችግሩን አሳሳቢነት ተረድተን ኃላፊነት በመውሰድ ሀገር ማዳን አለብን ብለዋል።

የኮሚሽኑ የሥነ ምግባርና የፀረ-ሙስና ስልጠና ስራ አስፈፃሚ አቶ ዳግም አላምረው የስልጠናው ዋና ዓላማ ሰልጣኞች በመንግስት ተቋማት ውስጥ በግዥ ላይ የሚፈጸምን ሙስና የመከላከል አቅምን በማሳደግ ከሙስና እና ብልሹ አሰራር የጸዳ የግዥ ስርዓት እንዲከተሉ ማስቻል መሆኑን ገልፀዋል።

ስልጠናው በግዥ ሂደት ላይ የሚፈፀም የሙስና ተዋናዮች፣ በመንግስት ግዥ ውስጥ ለሙስና ተጋላጭ የሚያደርጉ ሁኔታዎች፣ ከግዥ ባለሙያዎች የሚጠበቅ ስነምግባር እና በግዥ ሂደት ላይ ጠቋሚ ሁኔታዎች እንዲሁም በሌሎች ርዕሶች ላይ ያተኮረ ሲሆን፤ ሰልጣኞች የተለያዩ ሀሳቦችን በማንሳት የጋራ ግንዛቤ የተፈጠረበት ስልጠና መሆኑን መገንዘብ ተችሏል።

በስልጠናው የማጠቃለያ ፕሮግራም ንግግር ያደረጉት የግዥና ንብረት ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተር አቶ ሀጂ ኢብሳ ኮሚሽኑ ለግዥ የስራ ኃላፊዎች ስልጠናው መስጠቱ ሙስናና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል አይነተኛ ሚና እንዳለው ገልፀዋል።

በሀገራችን ከሚበጀተው በጀት 70 ከመቶው የሚይዘው ለግዥ የሚውል መሆኑን አመላክተው፤ በገንዘብ ሲሰላ 560 ቢሊዮን እንደሆነ ገልፀዋል። ስለዚህ ግዥ ላይ ልዩ ትኩረት በማድረግ መሰራት አለብን ብለዋል።

በዩኒቨርሲቲዎች ሙስናና ብልሹ አሰራር መኖሩን ጠቅሰው፤ ቡሌሆራ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ በማንም ሰው ስም ያልተመዘገቡ እና አገልግሎት የማይሰጡ መኪኖች በየቦታው ወደቀው እንደሚገኙ አመላክተዋል።

ዳይሬክተሩ አክለውም ባለፈው አመት አርባምንጭ ዩኒቨርሲቲ በግዥ ስርዓት ችግር ውስጥ እንደነበር ገልፀው፤ ግዥ ላይ የሚሰሩ አመራሮችን በመቀየር ችግሩን ማስተካከል መቻሉን ጠቁመዋል።

በአሁኑ ወቅት ወደ ቴክኖሎጂ በመሸጋገር በግዥ ሂደት የሚባክነውን የሀገር ሀብት ለመቀነስ ጨረታዎች በኦንላይን ማካሄድ እንደተጀመረ ጠቁመው፤ ሀገራችን ከሌብነት የፀዳች እንድትሆን ግዥን ከእጅ ንኪኪ በማራቅ በጋራ መስራት አለብን ብለዋል።

የፌዴራል የስነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ምክትል ኮሚሽነር አቶ ወዶ አጦ ሙስና መጠኑ ይነስ እንጂ በሁሉም ተቋማት መኖሩን ገልፀው፤ ሁላችንም ሙስናን ከመናገር ባለፈ መታገል አለብን ብለዋል። በአሁኑ ሰዓት ህዝባችን በሙሰኞች ምክኒያት በኑሮ ውድነት እየማቀቀ መሆኑን በመገንዘብ ከልባችን መስራት ይኖርብናል ሲሉ ለሰልጣኞች አሳስበዋል።

ሌቦች የህዝብን ሀብት በመዝረፍ ንብረቱን ከሀገር ውጭ በማሸሽ የተመቻቸ ኑሮ በዱባይ፣ በቻይና እና በሌሎች ሀገሮች አድርገው፣ ህዝባችን በድህነትና በስደት እንዲገላታ ያደርጋሉ ብለዋል።

ስልጠናው የዘርፉን ክፍተት በመረዳት በየተቋማችሁ ሙስናና ብልሹ አሰራር ለመታገል ግንዛቤ በመፍጠር የተሻለ ስራ ለመስራት እንደሚያግዝ ምክትል ኮሚሽነር ጠቁመዋል።

# በጋምቤላ ክልል ብልሹ አሰራሮች የወለዷቸውን የመልካም አስተዳደር ችግሮች ለመፍታት በትኩረት ይሰራል





በጋምቤላ ክልል ሌብነትና ብልሹ አሰራሮች የወለዷቸውን የመልካም አስተዳደር ችግሮች ለመፍታት በትኩረት እንደሚሰራ የክልሉ ርዕሰ መስተዳድር አቶ ኡሞድ ኡጁሉ አስታወቁ።

የመልካም አስተዳደር ቅሬታዎችና አቤቱታዎች መፍታት በሚቻልባቸው ጉዳዮች ዙሪያ የክልል፣ የዞንና የወረዳ አመራሮች በጋምቤላ ከተማ ተወያይተዋል።

በወቅቱ ርዕሰ-መስተዳደር ኢሞድ ኡጁሉ፤ በክልሉ ሌብነትና ብልሹ አሰራሮች የወለዷቸው በርካታ የመልካም አስተዳደር ቅሬታዎችና አቤቱታዎች እየቀረቡ ናቸው ብለዋል።

በክልሉ በተለይም ከመሬት አስተዳደር፣ ከፍትህና ሌሎች አገልግሎቶች ጋር በተያያዘ ከህዝቡ ቅሬታዎች እየቀረቡ መሆኑን ተናግረዋል።

ለክልል የቀረቡትን ሳይጨምር ባለፉት ሁለትና ሶስት ዓመታት ከክልሉ 34 ያህል የመልካም አስተዳደር ቅሬታዎችና አቤቱታዎች ለፌዴራል መንግስት መቅረባቸውን ጠቅሰዋል።

የመልካም አስተዳደር እጦት የአንድ አስተዳደር ደካማነት መገለጫ መሆኑን በመገንዘብ በየደረጃው የሚገኙ የአመራር አካላት ችግሩን መፍታት በቁርጠኝነት ሊሰሩ ይገባል ብለዋል።

በተለይም የሌብነትንና የህግ ማስከበር ሂደቶችንና አሰራሮችን አንዳንድ አመራር በውል ያልተገነዘቡበት ሁኔታ መኖሩን ጠቁመው፤ በሰው ኃይል ቅጥርና ሌሎች አገልግሎት አሰጣጦች ላይ በአብዛኛው ቢሮዎች ችግሮች እንዳሉን ገልጸዋል።

በአካባቢው መፈታት የሚችሉ የመልካም አስተዳደርና የአገልግሎት ቅሬታዎችን እልባት በማስይሰጥ አመራር ላይ አዲስ በተቋቋሙ የፀረ-ሙስና ህግ አስከባሪዎች ጭምር እርምጃ የሚወሰድ ይሆናል ብለዋል።

የዕለቱ የውይይት መድረክም ዓላማም አመራሩ በሚነሱ ቅሬታዎች ዙሪያ የጠራ ግንዛቤ በመያዝ ወደ ስራ እንዲገባ ለማስቻል መሆኑን ርዕሰ መስተዳደሩ አስረድተዋል።

ከውይይቱ ተሳተፊዎች መካከል የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ምክትል ፕሬዚዳንት አቶ ኡቻላ ኡጁሉ በሰጡት አስተያየት፤ በተለይም ከመሬት አስተዳደር ጋር በተያያዘ ለፍርድ ቤቱ በርካታ አቤቱታዎች እየቀረቡ መሆናቸውን ተናግረዋል።

በክልሉ እየተነሱ ያሉትን የመልካም አስተዳደር ቅሬታዎች ለመፍታት የባለድርሻ አካላትን ተቀናጅቶ መስራት የሚጠይቅ ነው ብለዋል።

በወረዳ፣ በዞንና በክልል ደረጃ የሚፈቱ አንዳንድ ቅሬታዎች ወደ ፌዴራል መንግስት የሚሄዱበት አጋጣሚዎች መኖራቸውን ያመለከቱት ደግሞ ሌላው የውይይቱ ተሳታፊ የማጀንግ ዞን አስተዳደሪ አቶ አብረሃም ማይክል ናቸው።

ተገቢ ባልሆነ ምክንያት ወደ ፌዴራል የሚሄዱ ቅሬታዎች በየአስተዳደር እርከኑ ለመፍታት በትኩረት መስራት እንደሚገባ መናገራቸውን ከኢዜአ የተገኘው መረጃ ያመለክታል።

# በኢትዮጵያ ሙያዊ ስነ-ምግባርን ያከበረ የጤና አገልግሎት አሰጣጥ ስርዓት እንዲጎለብት በትኩረት እየተሰራ መሆኑ ተገለፀ

በኢትዮጵያ ሙያዊ ስነ-ምግባርን ያከበረ የጤና አገልግሎት አሰጣጥ ስርዓት እንዲጎለብት በትኩረት እየተሰራ መሆኑን የኢትዮጵያ ጤና አጠባበቅ ማህበር ገለጸ፡፡

የኢትዮጵያ ጤና አጠባበቅ ማህበር “የተቀናጀ የጤና ሙያ ሥነ ምግባር ትግበራ ፍትሃዊ ደህንነቱን ለጠበቀና ሁሉን ተደራሽ ለሚያደርግ የጤና አገልግሎት” በሚል መርህ ከባለድርሻ አካላት ጋር ውይይት አካሂዷል፡፡

የማህበሩ ዋና ዳይሬክተር ዶክተር አለማየሁ መኮንን እንዳሉት፤ የጤና አገልግሎት ከህብረተሰቡ ጋር የተያያዘ በመሆኑ ከህዝቡ የሚቀርቡ ቅሬታዎችን በመሰብሰብና ምርምራ በማድረግ በህግ ተጠያቂ የሚሆኑበት አሰራር ተዘርግቷል ብለዋል፡፡

በተለይም ከሁለት ዓመት ወዲህ የቴክኒክ ኮሚቴ በማዋቀር የጤና ባለሙያዎች በህክምና አገልግሎት አሰጣጥ ወቅት የሚፈፅሙትን የሥነ ምግባር ጉድለት በመመርመር ህጋዊ እርምጃ እየተወሰደ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

የጤና ባለሙያዎች በህክምና ወቅት ተገልጋዩን በቅንነት ከማስተናገድ ጀምሮ የህክምና መመሪያዎችን እስከመስጠት ባለው ሂደት ሙያዊ ሥነ ምግባራቸውን አክብረው መስራት ይገባቸዋል ብለዋል፡፡

በመሆኑም የተገልጋዩን ቅሬታና በጤና ተቋማት የተፈጠረውን ሙያዊ ሥነ ምግባር ግድፈት በመመርመር ከቃል ማስጠንቀቂያ ጀምሮ የሙያ ፈቃዳቸውን እስከማገድ የሚደርስ እርምጃ ተወስዷል ብለዋል፡፡

በአዲስ አበባ ዩቨርሲቲ የጤና ሳይንስ ኮሌጅ የህግ ባለሙያ አቶ ዳንኤል ሰሎሞን በበኩላቸው፤ የጤና ባለሙያዎች በህክምና ወቅት በታካሚዎች ላይ በሚያደርሱት አካላዊ እና ሥነ-ልቦናዊ ጉዳት በህግ ተጠያቂ ይሆናሉ ብለዋል፡፡

በመሆኑም የጤና አገልግሎት ሥነ ምግባር ጉድለት የሚፈፅሙ ባለሙያዎች ጉዳያቸው በሥነ ምግባር ደንብ ብሎም በፍታህቤር እንደሚታይ ገልጸዋል፡፡

ከዚህም ባለፈ ማንኛውም የህክምና ባለሙያ ተገቢ የህክምና አገልግሎት ባለመስጠትና በከባድ ቸለልተኝነት በታካሚው ላይ ጉዳት ካደረሰ በወንጀል ይጠየቃል ማለታቸውን ከኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት ያገኘነው መረጃ ያመለክታል፡፡

# የገቢዎች ሚኒስቴር በግማሽ ዓመት ብቻ 4.1 ቢሊዮን ብር ዋጋ ያላቸው ሀሰተኛ ደረሰኞችን በምርመራ ማግኘቱን አስታወቀ

የገቢዎች ሚኒስቴር ባለፈው ስድስት ወራት “በጥናት በተለዩ” ድርጅቶች ላይ ባደረገው የምርመራ ኦዲት 4.1 ቢሊዮን ብር ዋጋ ያላቸው ሀሰተኛ ደረሰኞችን እንዳገኘ አስታወቀ።

ሚኒስቴሩ ህገ ወጥ ደረሰኝ በግብር ስርዓቱ ላይ ችግር እንደፈጠረበት እና ይሄንን ለመከላከል የሚደረገው “ቅንጅታዊ አሰራር የተወሰነ ጉድለት” እንዳለበት ገልጿል።

ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ይህንን ያስታወቀው የስድስት ወራት አፈጻጸሙን አስመልክቶ በሰጠው ጋዜጣዊ መግለጫ ላይ ነው።

መግለጫውን የሰጡት ሚኒስትሯ ወ/ሮ አይናለም ንጉሴ፤ ግብር ለመሰወር ሲባል “ግብይት ሳይፈጸም እንደተፈጸመ ተደርጎ” የሚቀርቡ ሀሰተኛ ደረሰኞች በግማሽ ዓመቱ ውስጥ ከታዩ ችግሮች መካከል እንደሆነ ለጋዜጠኞች ተናግረዋል።

ተቋሙ ባለፈው ስድስት ወራት ውስጥ ባካሄደው ጥናት ከለያቸው ድርጅቶች መካከል በ168 ያህሉ ላይ የምርመራ ኦዲት ማድረጉን አስታውቋል።

በተካሄደው የምርመራ ኦዲትም 4.1 ቢሊዮን ብር ዋጋ ያላቸው 2,851 ሀሰተኛ ግብይት ደረሰኞችን ማግኘቱን ገልጿል።

የገቢዎች ሚኒስቴር የስድስት ወራት አፈጻጸሙን አስመልክቶ ባዘጋጀው ማብራሪያ፤ የምርመራ ኦዲት የተደረገባቸው ድርጅቶች ሀሰተኛ ደረሰኞቹን “ለታክስ ዓላማ” እንደተጠቀሙበት መረጋገጡን ከኢትዮጵያ ኢንሳይደር የተገኘው መረጃ ያመለክታል።



# የአማራ ክልል የፀረ ሙስና አስተባባሪ ኮሚቴ መግለጫ ሰጠ

የአማራ ክልል የሥነ ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር ሀብታሙ ሞገስ በክልሉ ውስጥ በተቋቋመው የአማራ ክልል የፀረ-ሙስና አስተባባሪ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት አስመልክተው መግለጫ ሰጥተዋል።

የአማራ ክልል የፀረ-ሙስና አስተባባሪ ኮሜቴ ከተቋቋመበት ቀን ጀምሮ እስካሁን ድረስ እቅድ በማቀድ በክልሉ ውስጥ እስከ ታችኛው መዋቅር ድረስ በማውረድ የፀረ-ሙስና ትግሉ እንዲቀጣጠል ማድረግ ተችሏል። በመሆኑም ህዝቡ የፀረ-ሙስና ትግሉ አካል ሁኖ በእውነትና በማስረጃ የተደገፈ ጥቆማ እንዲሰጥ በክልሉ ውስጥ በ3 ቦታዎች በአብክመ ሥነምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን፣ ፍትህ ቢሮ እና ፖሊስ ኮሚሽን ላይ ጥቆማ መስጫ ሳጥን የተቀመጠ መሆኑን ኮሚሽነር ሀብታሙ ሞገስ ገልፀዋል።

ኮሚሽር ሀብታሙ አክለውም እስካሁን ድረስ በጥቆማ መስጫ ሳጥኑ የተሰጡ ጥቆማዎች 12 ሲሆኑ፣ በነዚህም ምርመራ እንዲካሄድ ለሚመለከተው አካል ተላልፈዋል። ከአሁን በፊት የተሰጡ ከ70 ያላነሱ ጥቆማዎች ምርመራቸው ተጠናቆ ክስ እንዲመሰረት ለአቃቢ ህግ ተላልፈዋል። በባህርዳር ከተማ በተሰጡ ከ100 ያላነሱ ጥቆማዎች ላይ ፖሊስ ምርመራ እያካሄደ እንደሆነም በመግለጫቸው አንስተዋል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ እስካሁን በተሰጡ ጥቆማዎች ህዝቡ የሚበረታታ ቢሆንም ከአሁን በፊት የተሰጡ ጥቆማዎች የተወሰኑ በበቂ ማስረጃ ያልተደገፉ በመሆናቸው ምርመራ ለማካሄድ ከባድ ስለሆነ የተስተካከለ መረጃ እንዲሰጥ በመግለጫው ጠቁመዋል።

ስለሆነም በቀጣይ በሚኖረው የፀረ-ሙስና ትግል ህዝቡ ከቂም በቀል ነፃ ሁኖ በእውነትና በማስረጃ በማስደገፍ በክልሉ በተቀመጡ ጥቆማ መስጫ ሳጥኖች፣ በየ ዞኑ በተቋቋመው የፀረ-ሙስና አስተባባሪ ኮሚቴ፣ እንዲሁም በ9427 ነፃ የስልክ መስመር ላይ በአካልና በስልክ ጥቆማ መስጠት የሚቻል መሆኑን ከሚሽነር ሀብታሙ ሞገስ አክለው ገልፀዋል።

ስለሆነም ያለህብረተሰብ ተሳትፎ የፀረ-ሙስና ትግሉ ውጤታማ ስለማይሆን የክልሉ ህዝብ በእውነት እና በበቂ ማስረጃ በማስደገፍ ሀገርና ህዝብን ከብልሹ አሰራሮችና ከዘረፋ ለመታደግ ሁሉም የክልሉ ህብረተሰብ የድርሻውን ሊወጣ ይገባል በማለት ኮሚሽነር ሀብታሙ ጥሪ ማስተላለፋቸውን ከክልሉ የሥነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ድህረ-ገፅ የተገኘው መረጃ ያመለክታል፡፡

# ቆይታ



**የፌደራል፣ የክልልና የከተማ አስተዳደር የስነምግባር የፀረ-ሙስና ተቋማት በህግ የተሰጣቸውን ሙስናን የመከላከል ተልዕኮ በአግባቡ ለመወጣት የትውልድን የሥነምግባር እና የሞራል እሴቶች የመገንባት፣ በመንግስት ተቋማትና በህዝባዊ ድርጅቶች ውስጥ የሚስተዋሉ ሙስናና ብልሹ አሰራሮች እንዲለዩና እንዲፈቱ የማድረግ፣ ሀብት መመዝገብና ትክክለኛነቱን በማረጋገጥ በተቋማት የግልፀኝነትና የተጠያቂነት ስርዓት እንዲሰፍን ማድረግና የተለያዩ ባለድርሻ አካላትንና መላውን ህብረተሰብ የፀረ-ሙስና ትግሉ ባለቤት እንዲሆን ማስቻል ሲሆን፣ የቤንሻንጉል ጉምዝ ክልል የስነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ይህን ዓለማ አንግቦ ስራዎችን እያከናወነ ይገኛል፡፡**

**የ‹‹ፀረ-ሙስና›› ጋዜጣ የስድስተኛ ዕትም እንግዳችን የቤንሻንጉል ጉምዝ ክልል የስነምግባር የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር አቶ መንግስቱ ላሉ ናቸው፡፡ የ‹‹ፀረ-ሙስና›› ጋዜጣ ከኮሚሽነር መንግስቱ ላሉ ጋር ያደረገችውን ቆይታ ይዞ ቀርባለች፡፡ መልካም የንባብ ጊዜ...**

የ‹‹ፀረ-ሙስና›› ጋዜጣ፡- በሀገራችን የሙስናና ብልሹ አሰራር ተፅዕኖ ስራዎችን ለማከናወን አስቸጋሪ እንደሆነ ይስተዋላል፤ በእናንተ ክልል ምን ይመስላል?

አቶ መንግስቱ ላሉ፡- ሙስና እንደሚታወቀው የሀገርን ኢኮኖሚ የሚገታ አደገኛ ነቀርሳ የሆነ፤ የህግ የበላይነት እንዳይኖር በማድረግ የህግ የበላይነትን የሚሸረሽር፣ የስነምግባርና የሞራል ቀውስን የሚያስከትል፣ ህዝብ በመንግስት ላይ አመኔታ እንዳይኖር የሚያደርግ አደገና ወቅታዊ የሆነ የሰላምና የደህንነት ስጋት በመሆኑ እንደ ሀገር መታወጁ ግልፅ ነው፡፡ ይህን ተከትሎ በአሁኑ ወቅት እንደ ሀገርና ክልል ሁለተናዊ እድገት በማምጣት የብልፅግና ጉዞ ለማሳካት ሁሉም ክልሎች የፀረ-ሙስና ትግል እያደረጉ ነው፡፡

ከዚህ አንፃር የቤሻንጉል ጉምዝ ክልል ሀገራዊ አሳሳቢ ችግር የሆነውን ሙስና በክልሉ ላይ የሚስተዋል እስከሆነ ድረስ ትግሉን ከመንግሥት ጋር በጋራ በመሆን ከፍተኛ ቁርጠኝነት ተወስዶ መታገል ካልተቻለ ለሀገርና ለክልል እድገት ከፍተኛ አደጋ መሆኑን በመረዳት የፀረ-ሙስና ኮሚቴ ተደራጅቷል፡፡

ሀገራዊ ብሔራዊ የፀረ-ሙስና ኮሚቴ መደራጀቱን ተከትሎ፣ ሰባት አባላት ያሉበትን የፀረ-ሙስና ኮሚቴ ታህሳስ 04/2015 ዓ.ም የክልሉ መንግስት ማዋቀር ችሏል፡፡ ይህን ኮሚቴ ሲያደራጅ፣ እንደ ክልል የሙስናና ብልሹ አሰራር አሳሳቢ ደረጃ ላይ የደረሱ ዘርፎችን በጥናትና በመረጃ ላይ በተደረገው ዳሰሳ መነሻ በማድረግ የፀረ-ሙስና ትግል በክልሉ ላይ እንዲደረግ የተወሰ ነው፡፡

በተለይ በክልል ደረጃ አገልግሎት አሰጣጥ ጋር ተያይዞ ለህዝብ እረሮ ምንጭ የሆኑ፣ የመልካም አስተዳደር ችግር በመሆን ተገልጋይን በየጊዜው እያማረሩ ያሉበት ዘርፎች የተለየበት ሁኔታ ሲሆን፤ በዋናነት በገጠርና በከተማ መሬት ጋር ተያይዞ ህዝቡ ከፍተኛ የሆነ ምሬት ውስጥ ገብቷል፡፡

ስለዚህ የክልሉ መንግስት አንዱ ትኩረት ያደረገው ከኢንቨስተመት ጋር ተያይዞ የከተማና የገጠር መሬት ላይ ነው፤ እንዲሁም የማዕድን ፍቃድ አሰጣጥ ጋር ተያይዞ ፍቃድ ለመውሰድ ሲባል በየቦታው የሚመጡ ሀሰተኛ ሰነዶች ስላሉ በልዩ ሁኔታ ትኩረት ተሰጦ እየተሰራ ነው፡፡ ፍትህ አካባቢ/አደባባይ ላይ የሚሰጡ አስተማሪ ያልሆኑ ቅጣቶች ሲታይ ሙሰኞች/ሌቦች በቅሌታቸው ልክ አስተማሪ ቅጣት እየተሰጠ አይደለም፤ ይህ ደግሞ ዝም ብሎ የመጣ ሳይሆን፣ ሲስተሙ በብልሹ አሰራርና በሙስና የተተበተበ መሆኑን ከህብረተሰቡ የሚመጡ ጥቆማዎች ስላሉ የችገሩ አካባቢዎች ተለይተው እየተሰራ ይገኛል፡፡

በተጨማሪም የክልሉ መንግስት የስራ እድል ፈጠራ ጋር ተያይዞ ከንግዱ ዘርፍና ከንግዱ ማህበረሰብ አካባቢ ያሉ ዋና ዋና ችግሮች ተለይተው በቁርጠኝነት ተግባራዊ ምላሽ በሚያሰጥ መልኩ ለመስራት ቅድመ ዝግጅቶችን በማጠናቀቅ ወደስራ ውስጥ ተገብቷል፡፡

## የፀረ-ሙስና ኮሚቴ መቋቋም ለስነምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ሙስናና ብልሹ አሰራርን ለመቀነስና ተጠያቂነትን ለማስፈን አይነተኛ ሚና አለው



የ‹‹ፀረ-ሙስና›› ጋዜጣ፡- ከለውጡ በኃላ እንደ ክልል የስነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የተከናወኑ ተግባራት ምን ይመስላል? በተለይ ከሀብት ማስመለስ ጋር በተያያዘ የተከናወኑ ስራዎች ካሉ ቢገልፁልን?

አቶ መንግስቱ ላሉ፡- በክልል ደረጃ ከለውጡ በኃላ ያለው የፀረ-ሙስና ትግል በጥሩ ሂደት በመመራት አበረታች የሆኑ ስራዎች ተከናውነዋል፡፡ የክልሉ የስነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የተቋቋመበትን አዋጅ እንደገና እንዲሻሻል ከተደረገ በኋላ ተቋማዊ አደረጃጀቱ ውስጣዊ አቅም እንዲኖረው ከማድረግ አኳያ ትኩረት ተደርጎ ተሰርቷል፡፡ አዋጁ እንዲሻሻል ምክኒያት ከሆኑት መካከል ሀብት በማስመዝገብ ሂደት ውስጥ የሚሸሹ ሀብቶችን አስቀድሞ ለመከላከል የሚያስችል የህግ ማዕቀፍ እንዲካተት ተደርጓል፡፡ አስቀድሞ ሀብት የማሳገድ ስልጣን ለስነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ማድረግ መቻሉ ትልቅ ስኬት ነው፡፡

ከሀብት ማስመዝግብ ጋር ተያይዞ በርከት ያሉ የተወሳሰቡ ችግሮች ያሉ ቢሆንም ከፋይዳ አንፃር ብዙ ጥቅሞች መኖሩን መረዳት ችለናል፡፡ ሀብት ማስመዝገቡ በራሱ ግብ ባይሆንም፤ በክልሉ ላይ ከ35 ሺ በላይ የመንግስት ተሻሚዎችና ሰራተኞች ሀብታቸውን እንዲያስመዘግቡ ተደርጓል፡፡ በዚህ ሂደት ሀብት ማጣራት፣ ትክክለኛነቱን ማረጋገጥ መቻል አለበት በሚል የተጀመሩ ስራዎች አሉ፤ ከዚህ አኳያ ከነችግሩም ቢሆን የተመዘገበን ሀብት በማጣራት ለፍትህ አካላት የሚሄዱ ተግባራትን በመለየት ብዙ ስራዎች ተከናውነዋል፡፡

የ‹‹ፀረ-ሙስና›› ጋዜጣ፡- አሁን ላይ የተቋቋመው የፀረ-ሙስና ኮሚቴ እና የስነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ዋና አላማ ልየነትና አንድነት ምንድን ነው?

አቶ መንግስቱ ላሉ፡- በሀገራችን በሚገኙ በከተማ አስተዳደር እና በክልል ደረጃ የስነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን በማቋቋም የተለያዩ ስራዎች እየተከናወኑ ይገኛል፡፡ በአሁኑ ወቅት ደግሞ በፌደራል፣ በከተማ አስተዳደር እና በክልል ደረጃ የፀረ-ሙስና ኮሚቴ ተቋቁመው ሙሰኞች እየተለዩ ይገኛል፡፡ ስለሆነም በስነምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን እና አሁን በተቋቋመው የፀረ-ሙስና ኮሚቴ ጋር በተያያዘ ብዥታዎች ተፈጥሮ ይስተዋላል፡፡ የስነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ተቋም አፍርሶ በኮሚቴ የማደራጀት አዝማሚያ ተደርጎ እንደተወሰደ ግንዛቤ ያላቸው የህብረተሰብ ክፍሎች እንዳሉ ተስተውሏል፤ ይህ ትክክል አይደለም፡፡ ምክኒያቱም የበለጠ የመንግትን ትኩረት አግንተው የተቋማትን ስራ እንዲያግዝና እንዲያስተባብር የተቋቋመ ኮሚቴ እንጂ፣ ተቋማትን ለማፍረስ የተቋቋመ ኮሚቴ አይደለም፡፡

ተቋማት ከመደበኛ ስራቸው በላይ ከወቅታዊ ከፀጥታውና ከኑሮ ውድነቱ በተጨማሪ ስር የሰደደውን ሙስናን መታገል ለአንድ ተቋም የሚሰጥ ባለመሆኑ የመንግስት እገዛና ድጋፍ ያስፈልጋል ከሚል እሳቤ በመነሳት ተቋሙ የሚያከናውነውን ስራ በበለጠ ውጤታማ ለማድረግ፣ አፈፃፀሙን የተሻለ ለማድረግ እና ለማገዛ እንዲሁም ለማስተባበር የተቋቋመ ኮሚቴ እንጂ ተቋሙን ለማፍረስ እንደሆነና ተቋሙ እንደሌለ ተደረጎ የሚወሰደው ግንዛቤ ትክክል እንዳልሆነ እውነቱን መረዳት ያስፈልጋል፡፡ የተቋቋመው ኮሚቴ የመጡለትን ጥቆማዎች ከስሜትና ከቂም በቀል በፀዳ መልኩ በመለየትና በማደራጀት ለተቋሙና ለመርማሪው አካል በመስጠት የማስተባበር እና ውሳኔ መሰጠቱን የሚከታተል ኮሚቴ እንጂ የስነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽንን ለማፍረስ የተቋቋመ ኮሚቴ አለመሆኑን መረዳት ያስፈልጋል፡፡

የ‹‹ፀረ-ሙስና›› ጋዜጣ፡- የቤንሻጉል ጉምዝ ክልል ብዙ እምቅ ሀብት ያለው እንደሆነ መጠን፣ ኮሚሽኑ እና አሁን የተቋቋመው ኮሚቴ ቅንጅት ምን እንደሚመስል እና ህብረተሰቡ ምን እንዲያግዝ ትፈልጋላችሁ?

አቶ መንግስቱ ላሉ፡- የቤንሻጉል ጉምዝ ክልል በተፈጥሮ የታደለ፣ ብዙ ፀጋ ያለውና መልማት የሚችል ክልል ነው፡፡ ይህን ተፈጥሮ ያደለውን አጋጣሚ ተጠቅሞ የበለጠ የክልሉን እድገት ወደተሻለ ደረጃ ለማድረስ እያንዳንዱን የመንግስት አሰራሮች በዘርፉ ለሙስናና ብልሹ አሰራሮች ችግር አለባቸው ተብለው የተለዩ ተቋማትና ዘርፎች አሰራራቸውን ግልፅና ተጠያቂነት በተሞላበት መልኩ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡ አሰራሮቹ ህግን፣ መመሪያንና ደንብን በመከተል በግልፀኝነት የሚከናወኑ ከሆነ ስራዎች የቅሬታ ምንጭ እና በብልሹ አሰራር የተተበተቡ ሊሆኑ አይችልም፡፡

ሌላው የሙስና ትግል ሁለትዮሽ በመፍጠር አገልግሎት ሰጭና ተቀባይ በመካከላቸው ያለውን ግንኙነት የአገልግሎት መሰረት በማድረግ መስራት አለባቸው እንጂ፤ ጥቅም በመስጠት አገልግሎት የመውሰድ አይነት አዝማሚያ መኖር ስለሌለበት ህዝቡ በፀረ-ሙስና ትግሉ ላይ ከነበረበት ባህላዊ አባባል ‘’ሲሾም ያልበላ፣ ሲሻር ይቆጨዋል’’ ከሚል አይነት ስሜት በመውጣት አገልግሎቱን በትክክለኛው ሰዓትና ቦታ ያለምንም ጥቅም ማግኘት አለብኝ ብሎ መምጣት አለበት እንጂ፣ አስቀድሞ የእጅ መንሻ ይዞ እየመጣ የመንግስት ተቋማት አገልግሎት ባልተገባ መልኩ መፈፀም የለበትም፡፡ አገልግሎት ሰጭውም ተባባሪ ባለመሆን ሙሰኞችን መታገል ያስፈልጋል፡፡

በሙስና ትግል ውስጥ ከህዝብ አይንና ጆሮ የተደበቀ ነገር ባለመኖሩ ህዝቡ የማጋለጡን ስራ መከወንና ጥቆማውን መስጠት አለበት፡፡ እንደ ክልል 9080 አጭር ነፃ የስልክ መስመር እና የቴሌግራም እንዲሁም ሌሎች የጥቆማ መስጫ መንገዶች በመጠቀም ጥቆማውን መስጠት ይኖርበታል፡፡ ጥቆማዎች ከምንም አይነት ቂም በቀልና መጠላለፍ ነፃ መሆን አለባቸው ብለን እናምናለን፡፡ የህዝብ ጥቅምና አገልግሎት እየተጎዳ መሆኑን በባለቤትነት እንደ ዜጋ በደንብ ተገንዝቦ ጥቆማዎችን መስጠት አለበት፡፡ ይህ ሲሆን ህጉ ለጠቋሚዎች የፈቀደው ማበረታቻ እና የህግ ከለላዎች በመኖራቸው፤ የፍትህ ተቋም በበቂ ሁኔታና በተሟላ መልኩ የጠቋሚዎችን ህልውና ሊያስጠብቅ በሚችል መልኩ የህግ ከለላ የሚሰጥበት አግባቦች መኖር አለባቸው፡፡

በሙስና ትግል ውስጥ ማወቅ ያለብን ባለድርሻ አካል የሚባል ባለመኖሩ ሁሉም ባለቤት ነው፡፡ በየቦታው ተበታትነው ያሉ የፍትህ ተቋማት እና ሌሎች አካላትም አንድ ላይ በመሆን በቅንጅት ወጥ የሆነ አሰራር በመዘርጋት ትግሉን በተናበበ መልኩ የተደራጀ መረጃ ልውውጥ ላይ መሰረት ያደረገ መሆን ይኖርበታል፡፡ የክልሉ ህዝብ ከኮሚሽኑ ጋር በመተባበር መስራት ከተቻለ ክልላችን ለማንም መብቃት፣ መልማት እና የተሻለ መሰረተ ልማቶችን ማምጣት የሚችል ይሆናል፡፡

# ሳይቃጠል በቅጠል

## በተቋማት ላይ የሥነምግባርና የፀረ-ሙስና መከታተያ ክፍሎችን ማጠናከር ለፀረ-ሙስና ትግሉ የሚኖራቸው ፋይዳ

**ተስፋዬ ሻሜቦ**



የሀገራችን የሥነምግባር እና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን አወቃቀር የኢስያ ሀገር ከሆነችው የሆንግ ኮንግ ሞዴል ላይ የተወሰነ ማሻሻያዎችን በማድረግ የተቋቋመ እንደነበር ይታወቃል። የሆንግ ኮንግ የፀረ-ሙስና ተቋም ሥራውን የጀመረው እ.ኤ.አ 1974 ሲሆን፣ የተቋሙ ዋና ዓላማ ለሁሉም የማህበረሰብ አካላት የሥነምግባርና የሙስና መከላከል ሥልጠና የመስጠት፣ በመንግስት ተቋማትና የግል ዘርፍ ሙስና እና ብልሹ አሠራርን መከላከል እና የሙስና ወንጀል ጥቆማዎችን በመቀበል የመመርመርና ለዐቃቤ ህግ የማቅረብ ተግባራትን መሥራት ነው። የሙስና ወንጀል ላይ የመክሰስና የማስቀጠት ሥልጣን የተሰጠው ለሀገሩ የአቃቤ ህግ ሲሆን ተቋሙም ከፀረ-ሙስና ተቋም ውጭ የተዋቀረ ነው። የፀረ-ሙስና ተቋሙ ከተለያዩ ተቋማት በተወጣጡ የአማካሪ የቦርድ አባላት የበላይ ጠባቂነት የሚመራ ሲሆን፣ ለሙስና እና ብልሹ አሠራር መከላከል ሥራ ራሱን የቻለ አማካሪ ኮሚቴም አለው።

በተመሳሰይ የሀገራችን የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች አደረጃጀትም በኢስያና በአሜሪካ የመንግስት ተቋማት ውስጥ የተደራጁ የሥነምግባር መከታተያ ክፍል/የሥነምግባር ባለሙያዎች ተሞክሮን በመውሰድ እንደነበር ሰነዶች ያመለክታሉ። የሀገራቱ የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች እንደስማቸው በተቋማት ውስጥ ለአመራርና ሠራተኞች ተዘጋጅቶ ተግባራዊ የሚደረገውን የሥነምግባር ኮድ/መመሪያ በማዘጋጀትና ግንዛቤ በመፍጠር አፈፃጸሙን የመከታተል፣ የመገምገምና ውጤታማነትን ማረጋገጥ ትኩረት ሰጥተው ይንቀሳቀሰሉ፤ እንዲሁም በተቋማት ውስጥ ሙስና እና ብልሹ አሠራር ችግር እንዳይከሰት የመከላከል ሥራዎችንም ትኩረት ሰጥተው ይሰራሉ።

በተለይ በአሜርካ የሥነምግባር ባለሙያዎች የተቋማት የመንግስት ሠራተኞችና አመራሮች ሥራ ከመጀመራቸው በፊት የሥነምግባር ኮድ አሳትመው በመስጠትና በሰነዱ ላይ በቂ ግንዛቤ ማስጨበጫ ሥልጠና አፈፃፀሙን ትኩረት ሰጥተው ክትትልና ግምገማ ያካሂዳሉ። በየዓመቱ ደግሞ የተቋማት አመራርና ሠራተኞች የሥነምግባር የክፍል ሥልጠና በቋሚነት እንዲወስዱ ያደርጋሉ። በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ የሥነምግባር ሥልጠና ያልወሰደ የተቋም አመራርና ሠራተኞች ቅጣት ተበይኖበት በመክፈል ሥልጠና እንዲወሰዱ ይደረጋል።

በሀገራችን የሥነምግባር መመከታተያ ክፍሎች አደረጃጀት ከኮሚሽኑ ማቋቋም ጋር ተያይዞ የተጀመረ ሲሆን፣ በወቅቱ በመንግስት ተቋማት ውስጥ የሚመደቡት በምርጫ ነበር። የተቋም የበላይ አመራር ለሥነምግባርና ሙስና መከላከል ይጠቅማል ያለውን አመራር ወይም ሠራተኛ በሥነምግባር ባለሙያነት መርጦ እንዲሠራ ያደርግ ነበር። ይህ ተመርጦ የተመደበው የሥነምግባር መከታተያ ክፍል/ኦፊሰር በተቋም ውስጥ ከፌዴራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የሚተላለፉ መልዕክቶችን የማስፈጸም ሥራ ይሰራል። ለምሳሌ- የፌዴራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የሥነምግባር ሥልጠና መስጠት ሲፈልግ፣ የሥነምግባር መከታተያ ክፍል ለሥልጠናው ምቹ ሁኔታ እንዲፈጥር ይነገረዋል፤ እሱም የተባለውን ያደርጋል።

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የበላይ ጠባቂነት የሥነምግባር መከታተያ ክፍል ተግባርና ኃላፊነትን ይዞ የወጣው ደንብ ቁጥር 144/2000 ስለ ምደባ ግልጽ አቅጣጫ አስቀምጧል።

ደንቡ የሥነምግባር መከታተያ ክፍልን ዓላማ፣ ተግባርና ኃላፊነትን፣ የሥነምግባር መከታተያ የሚመደብ የሥነምግባር ሁኔታን፣ ለሥራው የሚጠይቀውን የትምህርት መስክ፣ የተቋም የበላይ አመራር ስለ ሥነምግባር መከታተያ ክፍል ስለሚኖረው ተግባርና ኃላፊነት፣ የሥነምግባር መከታተያ ክፍል ተጠያቂነትን በማስቀመጥ የወጣ ነበር። በዚህ ደንብ መሠረት የመንግስት መሥሪያ ቤቶችና የልማት ድርጅቶች ውስጥ የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች ተመድበው ወደ ሥራ የገቡ ቢሆንም በተፈለገው ልክ ተልዕኮ የማሳካት ሥራ ሰርተዋል ለማለት ግን ያስቸግራል። እዚህ ላይ በተቋም ውስጥ የሥነምግባርና የፀረ-ሙስና ተልዕኮ ከማሳካት ረገድ ውጤታማ የሆኑ እንዳሉ ሊዘነጋ አይገበም። በርግጥ ደንብ ይወጣ እንጂ በተቋማት የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች አመዳደብ ሁኔታ ጉራማይሌ ነበር።

አንዳንድ ተቋማት የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች ለመመደብ ፈቃደኛ እንደማይሆኑ፣ አንዳንድ ተቋማት ደግሞ ምደባ ቢያካሄዱም የሥራ ክፍሉ በቂ ሥራ የለውም በሚል እሳቤ ሌላ ስራ ደርበው የሚያሠሩ ሲሆን፤ አንዳንድ ተቋማት ደግሞ የሥራ ቦታና ለሥራ የሚያስፈልግ ቁሳቁስ አይፈቅዱም ነበር።

በደንቡ የተሰጠውን የሥነምግባር ግንባታና ሙስና መከላከል ተግባርና ኃላፊነት ለማስፈጸም በቁርጠኝነት በጣም ተግተው የሚንቀሳቀሱ፣ በዚህም በተቋም የበላይ አመራር የጥቃት ጡንቻ ያረፈባቸው እንዲሁም በሌብነት ሠንሰለት የተደራጁ ሌቦች የጥቃት ሰለባ የሆኑ፣ በተቋም ውስጥ ሙስናን በመከላከላቸው የተሸማቀቁ፤ በዚህም የኖሩበትንና የሚወዱትን ተቋም ጥለው እንዲወጡ የተደረጉ፣ ከነበሩበት የሥራ መደብ እንዲነሱ የተደረጉ ወይም ዝቅ ተደርገው የተመደቡ ወይም የምደባ ቦታ እንዲያጡ የተደረጉ፣ የአካል ጥቃት ጉዳትን በራሳቸውና በቤተሰቦቻቸው ላይ ጭምር ጉዳትን ያስተናገዱ በርካታ የዓላማ ጽናት ያላቸው የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች እንደነበሩ ፀሐፊው ያስታውሳል።

ኮሚሽኑም በተሟላ መልኩ ባይሆንም የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች በተቋሞቻቸው የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ተልዕኮ የማሳካት ሥራን በትጋት እንዲሠሩ ክትትልና ግምገማ ከማድረግ በተጨማሪ የአቅም ግንባታ ሥልጠናዎችን ሲሰጥ ቆይቷል።

የፀረ-ሙስና ትግል ተልዕኮ እንዲያሳኩ የአቅም ግንባታ ሥልጠና የሚሰጣቸው የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች በተሰጣቸው የአቅም ግንባታ ሥልጠና መነሻነት ተግባርና ኃላፊነት ለመወጣት በሚያደርጉት እንቅስቃሴ ሂደት ላይ በርካታ ችግሮች እንደሚገጥሟቸው የሚገልጹ ሲሆን፣ በሚያደርጉት የሥራ እንቅስቃሴ መነሻነት ከተቋም አመራር ጋር ሳይስማሙ ሲቀር ከቦታቸው ያለበቂ ምክንያት እንዲነሱ ወይም ከነበሩበት የሥራ አካባቢ በርቀት ተመድበው እንዲሠሩ ስለሚደረጉ፣ በተቋሞቻቸው ላይ ያለቸውን ቅሬታና አቤቱታ ለኮሚሽኑ ያቀርባሉ። ኮሚሽኑም ያለበቂ ምክንያት ከሥራቸው እንዲነሱ የተደረጉትን የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች ጉዳይ በመከታተልና ከተቋማት አመራር ጋር በመጋፈጥ ጭምር የሥነምግባር መከታተያ ክፍል ላይ ህገወጥ እርምጃ በመውሰድ በህግ እንዲጠየቁ የተደረጉ የተቋማት አመራሮች ነበሩ፤ ወደነበሩበት የሥራ ቦታ እንዲመለሱ ሲሠራ የቆየ ቢሆንም የኮሚሽኑን በቂ ዕገዛና ድጋፍ ባለማግኘታቸው ምክንያት ሥራቸውን የለቀቁ፣ ወደ ሌላ ሥራ ክፍል የተዛወሩ ወይም የጥቃት ሰለባ የሆኑም እንደነበሩ ማስታወስ ይቻላል።

እንዲሁም ከተቋሙ የበላይ አመራር ለሥራ አመቺ የሆነ የሥራ ቦታ ያልተሰጣቸው፣ ለአቀዱት ሥራ በጀት የማይመደብላቸው፣ የሥራ መሳሪያዎች ያልተሟላላቸው፣ ለሙስና መከላከል ሥራ ለቀረቡት የውሳኔ ሀሳብ የተቋም የበላይ አመራር ውሳኔ የማያገኙ፣ በተቋም ውስጥ በሌሎች አመራርና ሠራተኞች የተቋም የበላይ አመራር ጆሮ ጠቢና መረጃ አቀባባይ ተደርገው የሚወሰዱ የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎችም ነበሩ፤ አሁንም እንደሚኖሩ ይገመታል።

በሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች በኩል ደግሞ መጠኑ ባይበዘም የሥነምግባር ግንባታና ሙስና መከላከል ሥራን አቅደው የማይሠሩ፣ የተሠጣቸውን ተልዕኮ ለማሳካት ተግተው የማይቀሳቀሱ፣ የሙስና ጥቆማ መረጃዎችን ለማጣራት የሚፈሩ ወይም የዕውቀትና የክህሎት ክፍተት ያለባቸው፣ በተቋም ውስጥ በሚሰጡ ውሳኔዎች ላይ ራሳቸውን ነፃና ገለልተኛ የማያደርጉ ወይም በማኔጅመንት ኮሚቴ ወይም በኮሚቴ ሥራ ላይ በመሳተፍ የውሳኔ አካል የሚሆኑ፣ የሙስና መረጃ ጠቋሚዎችን ሚስጥር በጥንቃቄ የማይዙና ለቀረቡ የሙስና መረጃዎች ወቅታዊ ውሳኔ የማይሠጡ፣ በተቋም ውስጥ የፀረ-ሙስና ትግል ተልዕኮ በምን አግባብ ለማሳካት እንደሚንቀሳቀሱ በትክክል የማሳያውቁ፣ በተቋም የፀረ-ሙስና ትግል ላይ የተቋም የበላይ አመራርን ቀርበው የማያመከሩ ወይም የተቋም የበላይ አመራር ቢሮ ለመግባት የሚፈሩ፣ የእቅድ አፈፃፀም ሪፖርት የማያቀርቡ ወዘተ እንዳሉ በተለያየ ጊዜ የተካሄዱ የዳሰሳ ጥናት ሪፖርቶች ያስረዳሉ።

ስለሆነም ተቋም ለሙስና መከሰት ምቹና እርጥብ የሥራ አካባቢ ከሆነ የተቋሙን ሀብትና ንብረት ለመመዝበር፣ ለመስረቅ፣ ለማጭበርበር፣ በሥልጣን አለግባብ ለመጠቀም የመሳሰሉ ድርጊቶችን ለመፈጸም አልመው የሚንቀሳቀሱ ስላሉ በአማካይ 15 በመቶ የሚሆኑ የተቋማት አመራርና ሠራተኞች አጋጣሚውን በመጠቀም የሥነምግባር መከታተያ ክፍል የሥራ እንቅስቃሴን የበለጠ ለማኮላሸት ይሠራሉ፣ ሥራው ላይ ጥላሸት ይቀባሉ፣ አሉባልታዎችን ያናፍሳሉ፣ የበላይ አመራር ጥቃት ሰለባ እንዲሆን አልመውና አቅደው መረጃ የሌላቸውን ወሬዎች ያነፍሳሉ። እነዚህ ሰዎች በአንድ ወቅት ላይ እርጥብ የሥራ አካባቢ የሠሩ ከሆነ በሥራ ባልደረቦቻቸው ላይ የሙስና ጥቆማ መረጃ ሊሰጡ ይችላሉ። ሥነምግባር መከታተያ ክፍል እነዚህ ሰዎች ከመጥላትና ከመፍራት ይልቅ ለተልዕኮው መሳካት በጥንቃቄ ለመጠቀም ሁኔታዎች ማመቻቸት ይኖርበታል።

በተቋም ውስጥ የሥነምግባር መከታተያ ክፍል ሥራን የሚደግፉት በአማካይ 25 በመቶ የሚሆኑ ናቸው። እነዚህ የሥነምግባር መከታተያ ክፍል ሥራን በበጎ ጎኑ የሚወስዱ፣ የሚያበረታቱ፣ በሙስና ላይ የመዘፈቅ ምጣኔያቸው አነስተኛ የሆኑ፣ ባገኙት አጋጣሚ የሙስና መረጃ ጥቆማዎችን ስለሚያቀርቡ ለእነሱም አመቺ ሁኔታዎች መፍጠር ያስፈልጋል። ከሁለቱም ወገን ሳይሆኑ የሚኖሩትን አመራሮችና ሠራተኞች ደግሞ በአማካይ 60 በመቶ ስለሚሆኑ እነዚህን ሰዎች ለፀረ-ሙስና ትግል ተልዕኮ መሳካት ለመጠቀም በተደጋጋሚ የግንዛቤ ማስጨበጥ ሥራ መሥራት ይጠይቃል።

የተሻሻለው የፌዴራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 1236/2013 ላይ የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች ተጠሪነት ለኮሚሽኑ በመደረጉ የነበረባቸው የነፃነትና የገለልተኝነት ችግር የተፈታ ቢሆንም በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደግሞ የተጠሪነት ጉዳይ ወደ ተቋም እንዲመለስ በመደረጉ የሥራ ነፃነትና የገለልተኝነት ጥያቄ ውስጥ እንዲገባ አድርጎታል። ስለሆነም ውሳኔው በሥራ አፈፃፀም ላይ ያስከተከውን ችግር በጥሞና በመመልከት የተሰጠው ውሳኔ እንደገና እንደሚታይ ተስፋ ይደረጋል።

የሥነምግባር መከታተያ ክፍል ስያሜ በአዋጁ 1236/2013 የሥነምግባር መከታተያ ክፍል የሚል ሲሆን በአንዳንድ ተቋማት የሥነምግባር መኮንን፣ የሥነምግባርና ፀረ-ሙስና አመራር ወይም ባለሙያ፣ በአንዳንድ ክልሎች የሥነምግባር ኦፊሰር ሲሆን፣ በፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን የደረጃ አወሳሰንና ምዘና መሠረት ደግሞ የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ሥራ አስፈፃሚና ባለሙያ ስያሜ ተሰጧቸዋል። በዓለም አቀፍ ደረጃ የሥነምግባር ኦፊሰር የሚል ስያሜ ተቀባይነት አለው።

ከአዋጅ 1236/2013 መውጣት በኋላ ደንብ ቁጥር 144/2000 የተሻረ ህግ የሚል እንድምታ ያለው ሲሆን አዋጁን ለማስፈጸም በኮሚሽኑ የተዘጋጀው መመሪያ ለፍትህ ሚኒስቴር ቀርቦ ባይጸድቅም የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች በተቋማቸው ውስጥ የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም የሥነምግባር ግንባታና የሞራል እሴቶች ግንባታ ሥራ ለመሥራት የፊት ለፊት የሥነምግባር ግንባታና የሙስና መከላከል ሥልጠና መስጠት፣ የማህበራዊ ሚዲያዎች ላይ ሥነምግባር መከታተያ ክፍል ማህበራዊ ሚዲያ አካውንት በመክፈት የተቋም አመራር፣ ሠራተኞችና ተገልጋዮች አባልና ተከታይ እንዲሆኑ በማድረግ የሥነምግባር ግንዛቤ የሚፈጥሩና የሙስና መከላከል ክህሎትን የሚያሳድጉ መልዕክቶችን ማስተላለፍ፣ የውይይት አጀንዳዎችን በመቅረጽ የተቋም አመራር፣ ሠራተኛ እና ተገልጋይ አስተያየት እንዲሰጡበትና እንዲሳተፉ ማድረግ፣ የተቋም አመራርና ሠራተኞች የሥነምግባር ኮድ ማዘጋጀትና ተግባራዊነትን መከታተል፣ መገምገምና ውጤታማነትን ማረጋገጥ፤ የሥነምግባር ግንዛቤ የሚፈጥሩ ባነሮችን፣ በራሪ ወረቀቶችን፣ ፖስተሮችን፣ ብሮሸሮችን በመጠቀም መልዕክቶችን ማስተላለፍ፣ በየጊዜው የተቋም አመራርና

ሠራተኞች የሥነምግባር ሁኔታን በጥናት በመለየት መነሻ ደረጃ በመስጠት በየጊዜው በሚደረግ ስሌት ከመነሻ ደረጃ በላይ ዕድገት ከታየ ሙስና በተቋም ውስጥ መቀነሱንና የመነሻ ደረጃው ማሽቆልቆል ከታየ ደግሞ በተቋም ውስጥ ሙስና መጨመሩን ፍረጃ መስጠት እንዲሁም በሥነምግባራቸው አርአያ የሆኑ ሰዎችን ድርጊት በመቀመር በማህበራዊ ሚዲያዎች ላይ ማስተላለፍና ሰዎችን የማበረታታት ሥራ መከናወን የሚጠበቅበት ነው።

በሌላ በኩል በተቋም ውስጥ ለሙስና እና ብልሹ አሠራር ተጋላጭ የሆኑ አሰራሮችን መከላከል ነው። በዚህ ዙሪያ በተቋም ውስጥ ለሙስና ሥጋት የሆኑ አሠራሮችንና አደረጃጀቶችን በዳሰሳ ጥናት መለየትና ለየሥራ ክፍሎች ለተለዩት የሙስና ሥጋቶች ደረጃ በመስጠት እንደየደረጃቸው ቅደም ተከተል የሙስና ቅነሳ ስትራቴጂ በማዘጋጀት በሚመለከታቸው የተቋሙ የሥራ ክፍሎች ተግባራዊ እንዲሆን መከታተልና ማረጋገጥ ነው።

በዚህም በተሠጠው ደረጃ ቅደምተከተል መሠረት የሙስና ሥጋት ያለባቸውን የሥራ ክፍሎች የሥራ መመሪያን በማሻሻል ወቅታዊ እንዲያደርጉ መከታተል፣ በተቋምና በሥራ ክፍል ውስጥ በታዩ የሥራ ድግግሞሽን የመቀነስና የማሻሻል ሥራ መሠራቱን፣ ለሥራ ክፍል የጥራት፣ የወጪ፣ የጊዜና የመጠን ስታንዳርድ እንዲዘጋጅ ማድረጉን፣ በሥራ ክፍል ውስጥ ለባለሙያዎች ግልጽ የሥራ ክፍፍል መኖሩን፣ አመራርና ሠራተኞች በዕቅድና በፕሮግራም የዓመት ዕረፍት የሚወስዱ መሆናቸውን፣ በተቋምና በሥራ ክፍል የታቀዱ ተግባራት በተቀመጠው መጠን፣ ጊዜ፣ ጥራትና ወጪ የሚከናወኑና የሚታይ ውጤት የተመዘገበ መሆኑን፣ የዲስፕሊን ጥሰት የሚያደርሱ አመራርና ሠራተኞች ህጋዊ በሆነው አስተዳደር ደንብ የሚጠየቁ መሆናቸውን፣ የተቋም ሂሳብና ንብረት ላይ ወቅታዊ የኦዲት ሥራ የሚሠራና ግኝት ላይ ወቅታዊ ማሻሻያ የሚደረግ መሆኑን፣ አንድ አመራር ወይም ሠራተኛ በአንድ ሥራ ቦታ ላይ ለበርካታ ዓመታት የማይሠራ መሆኑን እንዲሁም በሥራ ክፍል አመራርና ሠራተኞች መካከል ጤናማ የሥራ ክፍል መሠረት ያደረገ የሥራ ግንኙነት መኖሩን ወዘተ ማረጋገጥ ያስፈልጋል።

እንዲሁም በተቋም ሥራ ክፍሎች የሥራ እንቅስቃሴ ላይ ሊፈጸም የታሰበ ሙስና ወደ ሙስና ወንጀል ድርጊት ከመለወጡ በፊት እንዲቆም የማስደረግ ሥራ መሥራት የሥነምግባር መከታተያ ክፍል ሚና ነው። ስለሆነም በግዥ አፈፃፀም፣ በሰው ኃይል ቅጥርና ምደባ፣ በሥልጠና አሰጣጥ፣ በጥናትና ምርምር ሥራዎች፣ በንብረት አያያዝና አጠቃቀም በመሳሰሉት አካባቢዎች ሊፈጸም በሂደት ላይ የነበሩ የሙስና ችግሮችን ላይ ጥቆማዎች ለመቀበል የጥቆማ መቀበያ ቦታዎችን፣ ዘዴዎችን፣ አሠራሮችን በማመቻቸት (የጥቆማ ሣጥን፣ ስልክ ቁጥር፣ ማህበራዊ ሚዲያ አካውንት መክፍት) ማስተዋወቅ፣ ግንዛቤ መፍጠርም ይጠበቃል።

ይህ ሥራ በባህሪው አስቸኳይ ሙስና መከላከል ሥራ መሥራትን የሚጠይቅ ስለሆነ ጥቆማው የቀረበበት ድርጊት ወደ ሙስና ወንጀል ከመለወጡ በፊት ቶሎ በማስቆም ጉዳዩን በአስቸኳይ በማጣራት አስቸኳይ የማሻሻያ ሀሳብ ማመንጨት ይጠይቃል። ከዚህ ላይ የሥነምግባር መከታተያ ክፍል በደረሰው ጥቆማ ላይ የተቋሙን የበላይ አመራር በማማከር ድርጊቱን በአፈጣኝ በማስቆምና በማጣራት አስቸኳይ የማሻሻያ ሀሳብ በማመንጨት በተቋም የበላይ አመራር በኩል ለሚመለከተው የሥራ ክፍል ተደራሽ በማድረግ ተግባራዊነትን መከታተልና ማረጋገጥ ነው። ጉዳዩን ወዲያው ለኮሚሽኑ የማሳወቅ ግዴታ አለበት።

በአስቸኳይ የሙስና መከላከል አፈፃጸም ሂደት ላይ የተቋም አመራር ሚና ካነሰበት ጉዳዩን በአፈጣኝ በማቅረብ ወቅታዊ ምላሽ ማግኘት ያስፈልጋል። ከዚህ ላይ መታወቅ ያለበት ነገር ቢኖር የተቋም የበላይ አመራር ዕውቅና ሳይኖር ሥነምግባር መከታተያ ክፍል ብቻውን ሊፈጸም የታሰበውን የሙስና መረጃ ጥቆማ የማስቆም ሥራ መሥራት አይችልም።

ሌላው በሙስና ላይ የሚቀርቡ የጥቆማ መረጃ ዓይነቶች፣ ከጥቆማው ጋር ተያያዥ ስለሚደረጉ መረጃዎች፣ የጥቆማ ማቅረቢያ ዘዴ (በአካል፣ በስልክና በማህበራዊ ሚዲያ ሊሆን ይችላል)፣ የጥቆማ መስጫ ቦታና ጥቆማው ለማን፣ እንዴት እንደሚቀርብ ግልጽ የሆነ ግንዛቤ ጥቆማን ለሚያቀርቡ የሕብረተሰብ አካላት በግልጽ ማሳወቅና ግንዛቤ መፍጠር ከሥነምግባር መከታተያ ክፍል የሚጠበቅ ነው። ሊቀርቡ የሚችሉ ጥቆማዎች አራት አይነት ሊሆኑ ይችላሉ፤ የመጀመሪያው ሊፈጸም የታሰበ ሙስና ሲሆን፣ ይህን ጥቆማ ቀደም ሲል እንደተገለጸው ወደ ሙስና ወንጀል ድርጊት እንዳይለወጥ በፍጥነት የመከላከል ሥራ መሥራትን የሚጠይቅ ነው። ጥቆማው እንደታወቀ በፍጥነት ካልተሠራ ወደ ሙስና ወንጀል ድርጊት የመለወጥ ዕድሉ ከፍተኛ ስለሆነ የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች ጉዳዩን ለተቋም የበላይ ኃላፊ እና ለኮሚሽኑ በማሳወቅ ድርጊቱ እንዲቋረጥ አፈጣኝ የመፍትሄ ሀሳብ በማመንጨትና በማቅረብ ማስወሰን ነው። በማጣራት ሂደት ላይ ጥቆማ የቀረበው ጉዳይ ወደ ሙስና ወንጀል ድርጊት ከተለወጠ ወዲያው ለፖሊስ ወይም ለፍትህ ሚኒስቴር ማቅረብ ያስፈልጋል።

የተፈጸመ የሙስና ወንጀል ድርጊት ሆኖ ተጠርጣሪውን ከሥራ የማያስባርር ቀላል የሙስና ወንጀል ከሆነ የሥነምግባር መከታተያ ክፍል ጉዳዩን በማጣራትና የማሻሻያ ሀሳብ በማመንጨት ሪፖርት ለተቋም የበላይ ኃላፊ በማቅረብ ተግባራዊነትን መከታተል ነው።

የተፈጸመ የሙስና መረጃ ጥቆማ ሠራተኛው ወይም አመራሩን ከሥራ የሚያስበርርና ከባድ የሙስና ወንጀል ከሆነ የሥነምግባር መከታተያ ክፍል ጉዳዩን በመመዝገብ የመመርመርና የመክሰስ ሥልጣን ላለው አካል በአፋጣኝ በማስተላለፍ አፈፃፀሙን መከታተልና የተገኘውን ውጤት ለኮሚሽኑና ለጠቋሚው ማሳወቅ ነው።

አስተዳደራዊ ጉዳዮች ላይ የቀረበ ጥቆማ የሥነምግባር መከታተያ ክፍል ተልዕኮ ስላልሆነ በተቋሙ ላይ ጉዳዩ ለሚመለከተው የሥራ ክፍል መላክ ወይም ለህዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም በመላክ አፈፃፀሙን መከታተል ነው። በሁሉም ጥቆማ አግባቦች ላይ ስለተወሰዱ እርምጃዎች ላይ ለጠቋሚው ማሳወቅ ይገባል።

በተቋም ውስጥ የሀብት ማሳወቅና ምዝገባ ሥራዎችን መከታተል የሥነምግባር መከታተያ ክፍል ሚና አለው። በመንግስት ተቋማትና ህዝባዊ ድርጅቶች ውስጥ የሚገኙ አመራርና ሠራተኞች በህግ ሀብት የማስመዝገብ ግዴታ ስላለባቸው ያስመዘግባሉ። ስለሆነም ሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች ደግሞ ተቋሙ ውስጥ ነባር አመራሮችና ሠራተኞች ሀብታቸውን እንዲያስመዘግቡ ማስታወቂያ በመለጠፍ ጭምር ቅስቀሳ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል።

አዲስ ተሹመው ወይም ተመድበው ወይም ተቀጥረው ወደ ተቋሙ የሚቀላቀሉት አመራርና ሠራተኞች ደግሞ ሥራ ከመጀመራቸው በፊት ሀብታቸውን እንዲያስመዘግቡ ያደርጋል። ነባርም ሆነ አዲስ የተቋም አመራርና ሠራተኛ ሀብት በህጉ በተቀመጠው ጊዜ ሀብቱን ማስመዝገብ ካልቻለ ብር 1000(አንድ ሺ ብር) ቅጣት ከፍሎ እንዲያስመዝግብ፤ ለመክፈልና ለማስመዘገብ ፈቃደኛ ያልሆነው የሀብት አስመዝጋቢውን የተሟላ መረጃ የያዘ ሪፖርት በማዘጋጀት ለሥነምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ማስተላለፍ የሚጠበቅበት ሲሆን፣ ተቋም የሚለቁ አመራርና ሠራተኞች ሀብት ሳያስመዘግቡ ኪሊራንስ እንዳይወስዱ መከታተልም ዋና ሥራው ነው። ተቋሙን የሚለቁ አመራርና ሠራተኞች መልቀቂያ የሚሰጣቸው የሥነምግባር መከታተያ ክፍል ሲፈርም ብቻ መሆን አለበት።

በተቋሙ የኦዲት ግኝት የሙስና ሥጋት ምንጭ ስለሆነ በአፈጣኝ ማሻሻያ የማድረግ ሥራ እንዲሠራ እንዲሁም በተቋም የሚወሰዱ የዲስፕሊን እርምጃ ውሳኔ በትክክል ተፈጻሚ ስለመሆኑ መከታተልና ማረጋገጥም የሥነምግባር መከታተያ ክፍል ሥራ ነው።

ስለሆነም የሥነምግባር መከታተያ ክፍል በተቋም ውስጥ ነፃነቱንና ገለልተኝነት ለማረጋገጥ የማንኛውን ኮሚቴ አባል መሆን አይመከርም። የሥነምግባር መከታተያ ክፍል በተቋም ውስጥ በሚወሰኑ ውሳኔዎች ላይ የውሳኔ አካል ከሆነ ነፃና ገለልተኛ ሆኖ ለመንቀሳቀስ አይችልም። ስለሆነም የኮሚቴ ሥራ ከመሥራት መቆጠብ ይኖርበታል። የማኔጅመንት ኮሚቴ አባል በመሆን በሥነምግባርና ፀረ-ሙስና ላይ ለሚነሱ ጉዳዮች ማብራሪያ ከመስጠት ባለፈ በሚሰጠው ውሳኔ ላይ የውሳኔ አካል መሆን የለበትም። በማኔጅመንት ኮሚቴ አባል መሆን የሚቻለው ለመረጃ ቅርበት ብቻ ያለድምጽ በመሳተፍ ሊሆን ይገባል።

በተቋም የጥቅም ግጭት መከላከል ላይ የሥነምግባር መከታተያ ሚና ነው። ተቋም ውስጥ ለጥቅም ግጭት የሚያጋልጡ ጉዳዮችን በጥናት መለየትና የመከላከለያ ሀሳብ በማመንጨት ለተቋም የበላይ አመራር በማቅረብ ተግባራዊነት መከታተል ይጠበቅባታል። ለምሳሌ- አባቱ የሰው ሀብት አስተዳደር ኃላፊ ሆኖ ልጁ ወይም ዘመዱ ወደ ተቋም ለቅጥር ከመጣ አስተዳደሩ ዝምድና መኖሩን በመግለጽ ራሱን በግልጽ ማግለልና የቅጥር ሂደቱ ላይ ከአስተዳደሩ ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት የሌላቸው አካላት ተሳትፈው ቅጥር ሊፈጸም ይገባል። እንዲሁም ግዥ ሲፈጸም በወጣው ጨረታ ላይ የግዥ ኮሚቴ አባል የሆነ አመራር በጨረታ ዘመዱ ከተወዳደረ ይህን ለተቋሙ የበላይ አመራር በማሳወቅ ራሱን ከኮሚቴ አባልነት በማግለል የውሳኔ አካል መሆን የለበትም።

በተቋም ውስጥ የግዥ ፍላጎትና ዝርዝር መግለጫ ያዘጋጀ ባለሙያ ግዢው ሲፈጸም የቴክኒክ ኮሚቴ አባል ሆኖ እንዳይመደብ መከታተልም ያስፈልጋል። የክፍያ የሂሳብ ሠነድ ያዘጋጀው ባለሙያ ክፍያ የመፈጸም ሥራ እንዳይሠራ፣ የፋይናንስ ሥራ ክፍል እና የግዥ ሥራ ክፍል የሥጋ ዝምድና ያላቸው ወይም የጓደኝነት ትስስር ያላቸው ሰዎችን እንዳይሠሩ ወዘተ መከታተልና መገምገም ይጠበቃል።

በመጨረሻም በተቋማት ውስጥ የበላይ አመራር ለሥነምግባር መከታተያ ክፍል ዕገዛና ድጋፍ አያደርጉም የሚል ቅሬታዎች በተደጋጋሚ ይደመጣሉ። ለዚህ ችግር መንስኤው የተቋም አመራር የሥራ ክፍሉን ጠቀሜታ ካለማወቅ ሊመነጭ ይችላል።

በሌላ በኩል የሥነምግባር መከታተያ ክፍል ሥራ ክፍሉ ሊሰጥ የሚገባውን አገልግሎት በተገቢው ባለማስጠቱም ሊሆን ይችላል። ስለዚህ በቅድሚያ የተቋሙ አመራርና ሠራተኞች የሥነምግባር ሁኔታ እና የሙስና ሥጋት ሊሆን በሚችሉ አሰራርና አደረጃጀቶች ላይ ተጨባጭ መረጃዎችን በመያዝ የተቋሙን የበላይ አመራር ማማከር ከሥነምግባር መከታተያ ክፍል የሚጠበቅ ቅድመ ተግባር ነው። በመቀጠልም 'ሙስናን መታገል በተግባር' በሚል መርህ ለማሳካት የሚያስችል እቅድ በማዘጋጀት ማቅረብ ነው። በዚህም በተቋም ውስጥ ያሉ አመራሮችና ሠራተኞችን በሥነምግባር ኮድ/መመሪያ ማዘጋጀት፣ ለይስሙላ ሳይሆን የአመለካከት ለውጥ የሚያመጡ የሥነምግባር ግንባታ ተግባራትን ማከናወን፣ የሥራ ክፍሎችን የሙስና ሥጋት በመለየትና ደረጃ በመስጠት፣ የመከላከለያ ሀሳቦችን በማመንጨት እና ስትራቴጂ በማዘጋጀት፣ ፈፃሚ የሥራ ክፍሎችን ለይቶ በተጨባጭ ማቅረብ፣ በተቋም ውስጥ ሀብት ያስመዘገበውንና ያላስመዘገበውን ከነምክንያታቸው የሚያሳይ ተጨባጭ መረጃ በማዘጋጀት የሥራ ክፍሉ ጠቃሜታ ማሳየት ነው።

በተቋም ውስጥ የሆነውንና ያልሆነውን በበቂ መረጃና ማስረጃ ያልተደገፉ ጉዳዮችን ወደ ተቋም የበላይ አመራር ቢሮ መሄድ ሥራው ላይ እምነት እንዳይኖር ከሚያደርጉት አንዱ ነው። እንዲሁም በተቋም ውስጥ የተፈጸመውንና ያልተፈፀመውን አሉባልታዎችን የሚያናፍሱ ሰዎችን መረጃ በመያዝ ወደ ተቋም የበላይ አመራር ቢሮ መሄድ አያስፈልግም። የተናፈሱ አሉበልታዎችንና ወሬዎችን በበቂ መረጃ የተደገፉ ስለመሆናቸው በቅድሚያ በትክክል ማረጋገጥ የግድ ይሆናል። ወደ ተቋም የበላይ አመራር መድረስ ያለበት ጉዳይ በበቂ መረጃና ማስረጃ የተደገፈ ሲሆን ብቻ ነው። በተቋም ውስጥ አንዳንድ ሰዎች የግል ጥቅማቸውን ለማስከበር ያልተጨበጡ ጉዳዮችን በማጉላት የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች በማነሳሳትና በማሳሳት ወደ ተቋም የበላይ አመራር እንዲሄዱ ይገፋፋሉ፤ መጠንቀቅ ነው። ከዚህ ውጭ የተቋም የበላይ አመራር ለሥራ ክፍሉ ተገቢውን ዕገዛና ድጋፍ እንዲያደርግ በተቋም የሥነምግባር ግንባታና ሙስና መከላከል ላይ በምን አግባብ መታገዝ እንዳለበት በትክክል በማቀድ ተቋም ውስጥ የሙስና ሥጋት ያለባቸውን የሥራ ክፍሎች የሥራ እንቅስቃሴ ላይ ምን ዓይነት የክትትልና የግምገማ ሥራ እንደሚሠራ፣ የሥነምግባር ግንባታ በማን ላይ መሠራት እንዳለበት፣ በአጠቃላይ በተቋም ውስጥ ሙስናን ለመከላከል ብሎም ለመቀነስ ምን መሠራት እንዳለበት በማመልከት በግልጽ ማማከር ከሥነምግባር መከታተያ ክፍል የሚጠበቅ ዋነኛ ተግባር ነው።

የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች በኮሚሽኑ ባለሙያዎች ሥልጠና እንዲሰጥላቸው በተደጋጋሚ ይጠይቃሉ። በተቋም ውስጥ እንዲደራጅ የሚፈለገውና በፌዴራል የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን የተመዘነውና የፀደቀው የሥራ መደብ የሥነምግባርና የፀረ-ሙስና ሥራ አስፈፃሚ፣ የሥልጠና ባለሙያ፣ የሙስና ሥጋት ጥናት ባለሙያ እና የሙስና መረጃ ትንተና ባለሙያ የሥራ መደቦች ናቸው። በመሆኑም የሥልጠና ባለሙያ በኮሚሽኑ ጥራትና ተገቢነት በጠበቀ መልኩ የተዘጋጀውን የሥልጠና ማቴሪያል ወይም ሞጁል በመጠቀም የሥነምግባርና የሙስና መከላከል ሥልጠና መስጠት እንዳለበት ይጠበቃል። ይህን እንዲሠራ ደግሞ ኮሚሽኑ የአሰልጣኞች ሥልጠና ይሰጣል።

ኮሚሽኑ እንደሀገር የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና አስተባበሪ እንደመሆኑ መጠን የተቋማት የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች ሥልጠና ይሰጥልኝ ጥያቄ የሚያስተናግድ ከሆነ ከዋናው ሥራ በመውጣት ሥራው ተቋማዊ ስለሚሆን በውጤታማነት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ሊያሳድር ይችላል። ሌላው ቀደም ሲል የኮሚሽኑ የሥራ ባልደረባ የሆኑ ሰዎችን በመጋበዝ የሥነምግባር ግንባታና የሙስና መከላከል ሥልጠና እንዲሰጡ ማድረግም ከሠነዱ ጥራትና ተገቢነት አንፃር አግባብነት የሌለው ተግባር ነው።

በተቋማት ውስጥ የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች እያሉ ለምን ሙስና ይፈፃማል የሚሉ ጥያቄዎች ከህብረተሰቡ በተደጋጋሚ ይነሳል፤ ጥያቄው ትክክል ነው። የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች በተደራጀና በተጠናከረ መልኩ ተልዕኮ ለማሳካት በሚንቀሳቀሱት ተቋማት ውስጥ የሙስና ሥጋቶች የመቀነስ አዝማሚያዎች መኖራቸውን ጥናቶች ያመለክታል። በተቋም ውስጥ የተንዛዛ አገልግሎት አሰጣጦችን እንዲሻሻሉ፣ ለሙስና ሥጋት የሚፈጥሩ ህጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ወቅታዊና ግልጽ እንዲሆኑ ማድረግ፣ ከተገልጋይ የሚቀርቡ አቤቱታዎችና ቅሬታዎች ላይ ፍትሃዊ ውሳኔ እንዲሠጥ ማድረግ፣ የሙስና ሥጋት የሚሆኑ አሠራርና አደረጃጀቶች ላይ ተገቢ የሆነ የክትትልና የግምገማ ሥራ በተቋም የበላይ አመራር ጭምር በተጠናከረ መልኩ የሚሠራ ከሆነ ወዘተ በተቋም ውስጥ ሊከሰት የሚችል ሙስና ሊቀንስ የሚችልበት ዕድል ከፍተኛ ሲሆን፤ የተገለጹት ተግባራት በተገቢ መልኩ በማይከውኑ ተቋማት ውስጥ የሙስና ሥጋት ከጊዜ ወደ ጊዜ ሊያድግ ይችላል። እየሆነ ያለውም ይህ ነው።

ስለዚህ የተቋማት የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች የተልዕኮ ማሳኪያ ዕቅዶቻቸውን በትክክል በማቀድ ሥራዎቻቸውን ለተቋሙ ሠራተኞች፣ አመራሮች፣ የባለድርሻ አካላትና ተገልጋዮች ማሳወቅና ግንዛቤ መፍጠር ከቻሉ ሥራዎቻቸው በትክክል ከመታወቁም በላይ ተከታዮቻቸውን በብዛት የማፍራት ዕድሉ ከፍተኛ ሊሆን ይችላል።

በአጠቃላይ በተቋም ውስጥ የተደራጁት ትንንሽ ፀረ-ሙስና ኮሚሽኖች ተልዕኳቸውን ለማሳካት በንቃት፣ በትጋት፣ በዕውቀትና በክህሎት መንቀሳቀስ ከቻሉ በተቋም ውስጥ የሙስና መቀነስ አዝማሚያው ከፍተኛ ነው። ለዚህ ደግሞ የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች ራሳቸውን በዕውቀትና በልምድ በማበልጸግ የተጣለባቸውን ተልዕኮ በትጋትና በብቃት ለማከናወን ከተንቀሳቀሱ በተቋም ውስጥ ሙስና ይቀንሳል፣ በድምር ውጤት ደግሞ በሀገር ደረጃ ሙስና ሊቀንስ ይችላል።

የተቋማት የበላይ አመራሮች ለሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች በቂ ትኩረት በመስጠት ከሥራ ክፍሉ የሚቀርቡ የሥነምግባርና የፀረ-ሙስና ውሳኔ ሀሳቦችን በአውንታ በመቀበል ወቅታዊ ውሳኔ የመስጠት፣ ለሥራው ምቹ የሥራ አካባቢን መፍጠር፣ የሥራ ክፍሉን ዕቅድ አፈፃጸም የመከታተል፣ የመገምገምና ግብረ-መልስ የመስጠት ሥራዎችን በትኩረት ማከናወን ቢችሉ በተቋሞቻቸው ውስጥ በሥነምግባር የታነጸ አመራርና ሠራተኛ ይበዛል፣ የሙስና ሥጋት ይቀንሳል፣ ተቋሙ ያቀዳቸውን ሥራዎች አሟጦ በመተግበር ውጤታማ ይሆናል። በቆይታቸው ወቅት በማህበረሰቡና በተገልጋይ የተመሰገኑና የተወደዱ ይሆናሉ፤ ጥሩ ስምና ዝና ይኖራቸዋል። ስለሆነም የተቋም የበላይ አመራሮች የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎችን በተገቢው መንገድ ተጠቀሙባቸው ነው መልዕክቱ። ያወቀ ተጠቀመ።

የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎችም በቅድሚያ ሥራቸውን ለተቋማት የበላይ አመራሮችና ሌሎች ሥራ ኃላፊዎች በትክክል የማሳወቅ ኃላፊነት አለባቸው።

በአሁኑ ወቅት ኮሚሽኑ በአካሄደው የሪፎርም ሥራ የሙስና መከላከል ሥራ ላይ የአቅጣጫ ለውጥ በማካሄድ በዘርፍ ተኮር የሙስና መከላከል ሥራ ለማከናወን ተቋማትን በዘርፍ በማደራጀት ወደ ሥራ ገብቷል። የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎችም በተመሳሳይ በዘርፍ ተደራጅተው ትግሉን በቅልጥፍና እንዲመሩ ትስስሮች ተፈጥሯል። ይህን ሥራ በባለቤትነት የሚያስተባብር የሥራ ክፍል በመሪ ሥራ አስፈፃሚ ደረጃ አደረጅቷል።

በመሆኑም በፌዴራል ደረጃ በዘርፍ የተደራጁት ተቋማት የታቸኛውን ተዋርድ በመጠበቅ ክልል፣ ዞን እና ወረዳ ድረስ ባለው አደረጃጀት ያሉ የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎችን በአንድ ላይ በማደራጀት የፀረ-ሙስና ትግል በጋራ ማካሄድ ነው። ዘርፉን ተከትሎ ከፌዴራል እስከ ወረዳ ድረስ ያሉት የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች ተመሳሳይ የሥነምግባር ግንባታና ሙስና መከላከል ዕቅድ በማዘጋጀት ተግባራዊ እንዲያደርጉ፣ የዕቅድ አፈፃጸም ሪፖርቱንም የዘርፍ አደረጃጀትን በተከተለ ሁኔታ ከፌዴራል እስከ ወረዳ ድረስ በትስስር ከተደራጁት የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች በመሰበሰብና በማደራጀት ግምገማ ማካሄድ ነው። ይህም የዘርፍ ተኮር የሙስና ሥጋትን በመለየት የመከላከል ሥራዎችን በተቀናጀና በተደራጀ መልኩ ለማከናወን ያግዛል። ለምሳሌ ጤና ዘርፍ ውስጥ የተደራጁት ጤና ሚኒስቴርና ተጠሪ ተቋማት፣ በክልል ጤና ቢሮ፣ በዞን ጤና ጽ/ቤትና በወረዳ ጤና ጽ/ቤት የተደራጁ የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች በአንድ ተዋረድ አደረጃጀት በጋራ የሚያቅዱበት፣ ዕቅድ አፈፃፀም የሚገመግሙበት፣ መረጃ የሚለዋወጡበት የነበረው አሠራር በመልካም ተሞክሮ ልምድ የሚወሰድ ነው። በጤና ሚኒስቴር የተመደበ የሥነምግባር መከታተያ ክፍል ትስስሩን በበላይነት ያስተባብራል።

ስለሆነም ሌሎች ተቋማት የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎችም በተመሳሳይ መልኩ በዘርፍ ከፌዴራል እስከ ወረዳ ድረስ ተደርጅተው ወደ ተግባር እንዲገቡ የማድረግ ሥራ ትኩረት ተሠጥቶ መከናወን ይኖርበታል። ይህም በሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች መካከል ያለውን የአቅም ክፍተትን ለመሙላት፣ በዘርፉ የሚታየውንና የጋራ ጠላት የሆነውን ሙስና በጋራ ለመታገል፣ በሥነምግባር ግንባታና ሙስና መከላከል ወቅታዊ መረጃ ለመለዋወጥ ከማገዙም በላይ በሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች መካከል ህብረትን በመፍጠር ለፀረ-ሙስና ትግል መነሳሳት ከፍተኛ አስተዋፆ ስላለው በድምር ውጤት የሀገሪቱን የፀረ-ሙስና ትግል እንቅስቃሴ ያጠናክራል። በውጤቱም የፀረ-ሙስና ትግሉን በማላቅ የሀገሪቱን ብልጽግና ጉዞ እውን የማድረግ ሚናው የጎላ ነው።

# ከሙስና ምርመራ ዘገባ ማህደር

**በዚህ ዓምድ የተለያዩ ከሙስናና ብልሹ አሠራር አንፃር በሀገር አቀፍ ደረጃ የተከናወኑና ለህብረተሰቡ ከፍተኛ እውቀትና እውነተኛ መረጃ ይሰጣሉ ተብለው የሚታመኑና በሙስና ወንጀል የተመዘበረ የሀገር፣ የህዝብና የመንግስት ሀብት በማስመለስ ዙሪያ የተሰሩ ስራዎችንና ግንዛቤ የሚፈጠርበት እንዲሁም ሀገራችን ያፀደቀቻቸውንና እየተገበረች ያለቸውን የተለያዩ ዓለም ዓቀፍ፣ አህጉር ዓቀፍና ቀጠና ዓቀፍ ህጎችና አፈፃፀማቸውን አስመልክቶ የተሰሩና በመሠራት ላይ ያሉ ዋና ዋና ተግባራት አጠር ተደርገው የሚቀርቡበት ነው፡፡**

## የሙስና ወንጀል ምስክሮችና ጠቋሚዎች ጥበቃና ከለላ ምን ያህል ያውቃሉ? የሀገራችን ህግስ በዚህ ዙሪያ ምን ይላል?

በወንጀል ፍትህ አስተዳደር ስርዐት ውስጥ ቁልፍ ሚና ካላቸው ተግባሮች አንዱና ዋናው ወንጀለኞችን በተሟላ መልኩ በሠው፣ በሠነድ፣ በቴክኒክ፣ በህክምናና ሌሎች ተጨባጭ ማስረጃዎች ጥፋታቸውን በህግ ፊት በማስረዳትና በማረጋገጥ ለጥፋታቸው ተገቢውን ቅጣት እንዲያገኙ ማድረግ ነው፡፡ ይህ ተግባር የስራው ባለቤት የሆኑትን የምርመራ ፖሊሶችን ከሳሽና የተፈፀመውን ወንጀል በፍርድ ቤት የሚያስረዱ ዓቃቢያነ ህጎችን እጅጉን ከሚፈትኑ ስራዎች ዋናውና ግንባር ቀደሙ ነው፡፡

በተለይ እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ሀገሮችና የማስረጃ ህጋቸው ኋላቀር በሆነና እንደሌሎች ሀገሮች በዘመናዊ የምርመራ ሳይንስ የዳበረ ባልሆነባቸው ሀገራት የወንጀል ድርጊቶችን በተሟላ ማስረጃ አደራጅቶ ለፍርድ ቤት በማቅረብና ከበቂ ጥርጣሪ ውጭ/ beyond any reasonable dought / ፍርድ ቤቶችንና ዳኞችን አሳምኖ ወንጀለኞች ለፈፀሙት ጥፋት ተገቢውን የህግ ቅጣት እንዲወስኑ በማድረግ ዙሪያ ከፍተኛ ችግሮች ከመኖራቸውም ባለፈ የወንጀል ፍትህ ሥርዐቱን ዓቅምና ብቃት በመፈታተን በህብረተሰቡም ዘንድ እምነት እንዲያጣ ያደርገዋል፡፡

ይህን ስራ እጅግ ፈታኝ ከሚያደርጉ ምክንያቶች ውስጥ አንዱና ዋናው ወንጀለኞች የወንጀል ድርጊት የሚፈፅሙት እጅግ ጥንቃቄ በተሞላበትና በተቻለ ዓቅም ከምንም አይነት ማስረጃ በተሰወረ መንገድ በተደራጀ፣ በተጠናና በዕውቀት በዘመናዊ ቴክኖሎጂ ጭምር ተደግፎ መሆኑ ነው፡፡ የማስረዳት ስራውም የሚከናወነው ወንጀሉ ተፈፅሞ ካበቃ በኋላ ወደ ኋላ ተመልሶ ቀድሞ በስውር የተፈፀመ ተግባርን በማስረጃ አስደግፎ ማረጋገጥ በመሆኑ፤ እንደ እኛ ሀገር በዘመናዊ የስለላና የክትትል፣ የመረጃ፣ የፎቶ ካሜራና ሌሎች ስውር መከታተያ ሳይንሳዊ መንገዶች የሌሉባቸው ሀገራት በስውር የተፈፀመን የወንጀል ድርጊት ለፍርድ ቤት አቅርቦ ከበቂ ጥርጣሬ ውጭ ለማስረዳትና ዳኞች የወንጀል ድርጊቱን ከበቂ የአዕምሯቸው ጥርጣሬ ነፃና እርግጠኛ ሆነው በወንጀል ፈፃሚዎች ላይ ተገቢ ቅጣትና ፍርድ ለመስጠት ይቸገራሉ፡፡

ይህ ችግር ደግሞ የበለጠ ከባድና ውስብስብ የሚሆነው ከሌሎች መደበኛ የወንጀል ድርጊቶች በበለጠ የሙስና ወንጀል ድርጊትን በተሟላ ማስረጃ ለፍርድ ቤት ለማስረዳት አለመቻል ሲሆን፤ በሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታም ቀድሞ የፌደራል የሥነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የሙስና ወንጀሎችን የመመርመርና የመክሰስ ስልጣን እያለውም ይሁን አሁንም በፌደራል ፖሊስና በጠቅላይ ዓቃቤ ህግ እንደ ሀገር ሙሰኞችን ለፈፀሙት የሙስና ወንጀል በፍርድ ቤት ከበቂ ጥርጣሬ ውጭ በማስረዳትና ለፈፀሙት የሙስና ወንጀል ተጠያቂ በማድረግና በማስቀጣት እንዲሁም በሙስና ያፈሩትን ሀብት በማስመለስ ዙሪያ ከፍተኛ ሀገራዊ እንቅፋት ከመፍጠሩም ባለፈ በሀገራዊ የፀረ-ሙስና ትግል ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ ከመሆኑም ባለፈ የምርመራ ፖሊስ ተቋማትንና የከሳሽ የዓቃቢያነ ህግ ተቋማት ስራን እየተፈታተነ ይገኛል፡፡

በወንጀል ማስረጃ ሁኔታ ለግንዛቤ ያህል ይህን ካየን ስለዋናው ርዕስ የማስረጃና የጠቋሚዎች ከለላና ጥበቃ አስፈላጊነት እና በኢትዮጵያ ያለው ተጨባጭ ሁኔታ ምን ይመስላል የሚለውን ወደፊት በዝርዝር እንደምናስነብባችሁ ቃል እየገባን ለጊዜው የተወሰነ ግንዛቤ ለመስጠት የሚከተለውን ባጭሩ እናያለን፡፡

የወንጀል ምስክሮችና ጠቋሚዎች በወንጀል ፍትህ ስርዓት ውስጥ ከላይ እንደተገለፀው እጅግ ወሳኞችና ሀገራዊ የወንጀል መከላከልና መዋጋት ዙሪያ በተለይ የተፈፀሙ ወንጀሎችን በፍትህ አደባባይ በተሟላ ማስረጃ ከበቂ ጥርጣሬ ውጭ አረጋግጦ በማስረዳት ወንጀል ፈፃዎችን ለፈፀሙት ወንጀል ተጠያቂ እንዲሆኑ በማድረግ ዙሪያ እና ጠቋሚዎች በወንጀለኞች በረቀቀ እውቀትና ሰንሰለት በተደራጀ አኳኃን ከማስረጃ ዕይታ ውጭ በሆነ ሁኔታ የሚፈፅሙትን ስውር የወንጀል ድርጊት ለህግ አካላት በማሳወቅና በመጠቆም ዙሪያ በሀገራዊ የወንጀል መከላከልና መዋጋት ተተኪ የሌላቸው ቁልፍና ወሳኝ አካላት ናቸው፡፡ በመደበኛ ወንጀሎችም በሙስና ወንጀል ዙሪያ የሀገራችን ፍትህ ስርዓት እስካሁን ላከናወነው እና አሁን እያከናወነ ላለው እንዲሁም ወደፊት ለሚያከናውናቸው ስራዎች ዋና መነሻና መሠረት በመሆናቸው በዚህ ተግባር ላይ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ በሚሳተፉ የወንጀል ምስክሮችና ጠቋሚዎች ላይ የሚደርሰው የተደራጀና የረቀቀ ጥቃት ብዙዎቹን ከነቤተሰቦቻቸው ጭምር የሙሰኞች የተደራጀና የረቀቁ ቁሳቁሶች በመጠቀም፣ በገንዘብና በዕውቀት በተደራጀ ሁኔታ የጥቃት ሠለባ የሆኑና እስከ ህይወት ማጣት ድረስ የደረሰ ጥቃት የተፈፀመባቸው በተጨባጭ የሚታወቅ ነው፡፡

ለዚህ እንደዋና ክፍተት የሚታየው በሀገራችን ያለው የወንጀል ምስክሮችና ጠቋሚዎች ጥበቃና ከለላ ከመሠረቱ በጠንካራ ህግ የተደገፈ አለመሆኑ ሲሆን፤ ቀደም ሲል ለምስክሮች ጥበቃና ከለላ ተብሎ የወጣው አዋጅ ቁጥር 699/2010 ዓ.ም የጠቋሚዎችን ከለላና ጥበቃ ያላካተተ ከመሆኑም ባለፈ ራሱ ለምስክሮችና ቤተሰቦቻቸው ፈጣንና ጠንካራ የሕግ ጥብቅ ከለላና ጥበቃ የማያደርግ በመሆኑ ከህግ ያለፈ ተጨባጭ ትግበራ ስለሌለው የጉዳዩ አሳሳቢነት ታምኖበት እንደሀገር የሚመለከታቸው የፍትህ አካላት ከተወያዩበት በኋላ በተደረሰ የጋራ ስምምነት፣ ከዚህ ቀደም በአዋጅ ፀድቆ ስራ ላይ ያለው የወንጀል ምስክሮች አዋጅ እንደገና እንዲሻሻልና የወንጀል ጠቋሚዎችንም ጥበቃና ከለላ አካትቶ በተሻለ ሁኔታና ጠንካራ የከለላና ጥበቃ አዋጅ ሆኖ እንዲዘጋጅ በተወሰነው መሠረት የፌደራል ጠቅላይ ዓቀቤ ህግ፣ ፌደራል ፖሊስና የፌደራል የሥነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን እንዲሁም ሌሎች ተቋማትን ያካተተ የባለሙያዎች ቡድን ተዋቅሮ አዲስ የወንጀል ምስክሮችና ጠቋሚዎች አዋጅ ረቂቅ አዘጋጅቶ በህግ አውጪው ለማስፀደቅ የመጨረሻ ማጠናቀቂያ ላይ የደረሰ ሲሆን፤ በቅርብ ጊዜ ውስጥ ፀድቆ ወደ ስራ እንደሚገባ ይታመናል፡፡ የተከበራችሁ አንባቢያን ይህ ጉዳይ ሠፊ የህግና የፍልስፍና ማብራሪያ የሚፈልግና ለአንባቢዎችም እጅግ ጠቃሚ እውቀት የሚሠጥ መሆኑን ስለምናምን በቀጣይ የጋዜጣው እትም ሠፊ ማብራሪያ ይዘን የምንቀርብ ይሆናል፡፡

## የሙስና ወንጀል በመፈፀም ምርመራ ተደርጎባቸው ውሳኔ ያገኙ መረጃዎች እና በሂደት ያሉ መረጃዎች

በመሆኑም በፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ልደታ ምድብ 4ኛ የሙስና ጉዳዮች ወንጀል ችሎት ከ410 ሺህ በላይ የአሜሪካ ዶላር እንዲሸሽ አድርገዋል የተባሉ አራት የጉሙሩክ ሰራተኞችና ሦሥት አስመጪ ነጋዴዎች በሙስና ወንጀል ክስ ተመሰረተባቸው፡፡ ተከሳሾች አጠቃላይ ሰባት ሲሆኑ የጉሙሩክ ኮሚሽን ሰራተኞች የሆኑት ምትኩ አበባው፣ ወተቱ አበበ፣ ሊቁ ዘኮነ አለሙ እና ቤተልሔም ንጉሴ እንዲሁም አስመጪ ነጋዴዎች ናቸው የተባሉት ሮዛ ደፎ ቱሪ፣ ዮናስ ከበደ ደስታ እና ወንደሰን ተምትም አደራ ናቸው፡፡

የፍትህ ሚኒስቴር የሙስና ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ዐቃቤ ህግ በተከሳሾቹ ላይ አጠቃላይ ተደራራቢ ሰባት የሙስና ወንጀል ክሶችን ያቀረበባቸው ሲሆን፤ ከአንደኛ እስከ አራተኛ ተራ ቁጥር የተጠቀሱ ተከሳሾች በጉሙሩክ ኮሚሽን ሲሰሩ ከ4ኛ እስከ 7ኛ ተራ ቁጥር የተጠቀሱ ነጋዴዎች 410 ሺህ 820 የአሜሪካ ዶላር በተለያየ ጊዜ ከውጭ ይዘውት የገቡት ነው በማለት እና ዲክሌር በማድረግ ከነጋዴዎቹ ጋር በመመሳጠር ሀገሪቱን የውጭ ምንዛሬ በማሳጣትና ጉዳት በማድረስ ተደራራቢ በሙስና ወንጀል ክስ ቀርበባቸዋል፡፡ ቀሪዎቹ ነጋዴ ተከሳሾች ደግሞ የተጠቀሰውን የአሜሪካ ዶላር በማሸሽ እና በተወሰኑ ዶላሮች ደግሞ እቃ በመግዛት በሀገሪቱ ላይ ጉዳት በማድረስ ሙስና ወንጀል እና በህገወጥ መንገድ የተገኘ ገንዘብን ህጋዊ አስመስሎ መጠቀም ወንጀል ክስ ተመስርቶባቸዋል፡፡

ከ3ኛ እስከ 7ኛ ተራ ቁጥር የተጠቀሱት ተከሳሾች ከሰዓት በኋላ ችሎት ቀርበው ክሱ እንዲደርሳቸው ከተደረገ በኋላ ክሱ በንባብ ተሰምቷል፡፡ ፍርድ ቤቱ ቀሪ 1ኛ እና 2ኛ ተከሳሾች ፖሊስ መጥሪያ እንዲያደርስና በቀጣይ ቀጠሮ እንዲቀርቡ ትዕዛዝ በመስጠት የቀረቡ ተከሳሾች ግን የክስ መቃወሚያ ካላቸው ለመጠባበቅ ለየካቲት 2 ቀን 2015 ዓ.ም ተለዋጭ ቀጠሮ መሰጠት ችሏል፡፡

በሌላ መረጃ አምስት ስራ አስኪያጆችን ጨምሮ ዘጠኝ ተከሳሾች ከ87 ሚሊየን ብር በላይ ጉዳት ማድረስና ሰነዶችን በማጥፋት የሙስና ወንጀል ክስ የቀረበባቸው ሲሆን፤ 2 የባንክ ቅርንጫፍ ስራ አስኪያጆች እና 3 የግል ድርጅት ስራ አስኪያጆችን ጨምሮ 9 ተከሳሾች ከ87 ሚሊየን ብር በላይ ጉዳት ማድረስና ሰነዶችን በማጥፋት የሙስና ወንጀል ክስ እንደቀረበባቸው የፍትህ ሚኒስቴር አስታውቋል፡፡

የሙስና ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት በተከሳሾቹ ላይ በየተሳትፎ ደረጃ መጠን ጠቅሶ 6 ተደራራቢ የሙስና ወንጀል ክሶችን እንዳቀረበባቸው ተገልጿል፡፡ ክሱ የቀረበው በፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት 1ኛ የሙስና ጉዳዮች ወንጀል ችሎት ነው ተብሏል፡፡ ተከሳሾቹ 1ኛ የወጋገን ባንክ ሀያት ቅርንጫፍ ስራ አስኪያጅ የነበሩት መስፍን ገ/መድህን እና 2ኛ ሲኤሚሲ ቅርንጫፍ ስራ አስኪያጅ ሀይላይ ገ/ሚካኤል መሆናቸው ተጠቅሷል፡፡ 3ኛ እና 4ተኛ ተከሳሾች የኮንኮርዲያ ትሬዲንግ ስራ አስኪያጆች የነበሩት አቶ ኤርሚያስ ስዩምና አቶ ሄኖክ ፈለቀ እንዲሁም 5ኛ ተከሳሽ ኮንኮርዲያ ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግል ማህበር ናቸው፡፡ 6ኛ ተከሳሽ የአዲስ ዋይ ቴክኖሎጂ ስራ አስኪያጅ አቶ ፍሬው ዘውዱ፣ 7ኛ ተከሳሽ አቶ አብዱልቃድል አንዋር የፍሬው ዘውዱ ወኪል እንዲሁም 8ኛ ተከሳሽ የኢኤስ ቢኤች ትሬዲንግ ስራ አስኪያጅ ፍቅረማርያም ገብሩ እንዲሁም 9ኛ ተከሳሽ ኢኤስ ቢኤች ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግል ማህበር ናቸው፡፡

1ኛ ተከሳሽ የባንኩ ስራ አስኪያጅ ሆኖ ሲሰራ ከኮንኮርዲያ ትሬዲንግ ማህበርና የማህበሩ ስራ አስኪያጆች ከሆኑት ከ3ኛ እና ከ4ኛ ተከሳሾች ጋር በመመሳጠር ወንጀሉን እንደፈጸሙት ተገልጿል፡፡ የባንኩን መመሪያ በመተላለፍ የተሰጠውን ስልጣን ያለአግባብ በመገልገል በነሀሴ 12 ቀን 2013 ዓ/ም ለ3ኛ፣ 4ኛ እና ለ5ኛ ተከሳሶች ለእያንዳንዳቸው የ6 ሚሊየን 500 ሺህ ብር ሲፒዮ አዘጋጅቶ እንደሰጠ ተጠቅሷል፡፡ በተለያዩ ቀናቶች 34 ሚሊየን 617 ሺህ 700 ብር ገንዘብ ሲፒዮ በአንደኛ ተከሳሽ ተዘጋጅቶ ለ6ኛ እና ለ7ኛ ተከሳሾች የተሰጠ መሆኑን ዐቃቤ ሕግ ጠቅሶ፣ በከባድ የሙስና ወንጀል ክስ መስርቶባቸዋል፡፡ እንዲሁም 2ኛ፣ 3ኛ፣ 4ኛ፣ እና 5ኛ ተከሳሾች በቀረበባቸው የሙስና ወንጀል ክስ እንደተመላከተው፤ 2ኛ ተከሳሽ ስራ አስኪያጅ ሆኖ ሲሰራ ከባንኩ መመሪያ ውጪ 32 ሚሊየን 500 ሺህ ብር ሲፒዮ አዘጋጅቶ እንደሰጠ ተገልጿል፡፡ በ2ኛ፣ በ8ኛ እና በ9ኛ ተከሳሾች ላይ በቀረበባቸው ክስ እንደተመላከተው፤ 2ኛ ተከሳሽ ባዘጋጀው የ14 ሚሊየን ብር ሲፒዮ 8ኛ እና 9ኛ ተከሳሾች በመውሰድ የአየር ሰዓትና የሚፋቅ የሞባይል ካርድ ከኢትዮ ቴሌኮም ግዢ ፈጽመዋል፡፡ ተከሳሾቹ ከአሰራር ውጪ የተዘጋጀ ሲፒዮ በመውሰድና 87 ሚሊየን 617 ሺህ 700 ብር ጉዳት ማድረስ ሙስና ወንጀል ተከሰዋል፡፡ በተጨማሪም 1ኛ እና 2ኛ ተከሳሶች፤ በተለያዩ ቁጥሮች የተመዘገቡ ስድስት ሲፒዮዎችን በማጥፋት፣ የህዝባዊ ድርጅት ሰነዶችን በማጥፋት በባንኩ ላይ ከባድ ጉዳት በማድረስ ሙስና ወንጀል ክስ ቀርቦባቸዋል፡፡

የክስ መቃወሚያ ካላቸው ለመጠባበቅ ለየካቲት 11 ቀን 2015 ዓ/ም የተቀጠረ ሲሆን፤ የፌደራል ፖሊስ ላልቀረቡ ቀሪ አምስት ተከሳሾች መጥሪያ እንዲያደርስና በቀጣይ ቀጠሮ ተከሳሾቹ እንዲቀርቡ መታዘዙን መረዳት ተችሏል፡፡

በሌላ በኩል ከ6 ሚሊየን የአሜሪካ ዶላር በላይ በ26 ግለሰቦች እንዲሸሽ በማድረግ የተጠረጠሩ ሥድስት የጉምሩክ ሠራተኞች ላይ የክስ መመስረቻ ጊዜ መፈቀዱ የተገለፀ ሲሆን ክስ የሚመሠረትባቸው ግለሰቦች የሀገሪቱን የውጭ ምንዛሬ ማሳጣታቸው ተመልክቷል፡፡

ዐቃቤ ሕግ በሥድስቱ የቦሌ ኤርፖርት ቅርንጫፍ የጉምሩክ ኮሚሽን ተጠርጣሪ ሠራተኞች ላይ የሙስና ወንጀል ክስ ሊመሰርት መሆኑን ለፍርድ ቤቱ መግለጹን ተከትሎ ነው የክስ መመስረቻ ጊዜ የተፈቀደው፡፡ ሥድስቱ ተጠርጣሪዎች፥ ምትኩ አበባው፣ ግርማ ይባፋ፣ እንግዳ አቦ፣ ማቲዎስ ከታ፣ ቤተልሔም ንጉሴ እንዲሁም ሜላት መስፍን መሆናቸው በክሱ መረጃ ተመላክቷል፡፡ ተጠርጣሪዎቹ 26 ግለሰቦች በተለያየ ጊዜ ከውጭ ሀገር ይዘው የገቡት የአሜሪካ ዶላር ነው በማለት «ዲክሌር» ማድረጋቸውም ተመልክቷል፡፡ በየደረጃው ከፍተኛ ቁጥር ያላቸውን የገንዘብ መጠን ቀንሶ፣ ሰርዞና ደልዞ ሲስተም ላይ በማስቀመጥ እንዲሁም ሠነድ በመሰወር በአጠቃላይ ከ6 ሚሊየን በላይ የአሜሪካ ዶላር በግለሰቦቹ እንዲሸሽ አስደርገዋልም ተብለው በመጠርጠራቸው ምርመራ ሲከናወንባቸው እንደነበር መዘገቡ ይታወሳል፡፡

በተጠርጣሪዎቹ ላይ የምርመራ ሥራውን ሲያከናውን የቆየው የፌደራል ፖሊስ መርማሪ÷ ምርመራውን ማጠናቀቁን እና የምርመራ መዝገቡን ለዐቃቤ ሕግ ማስረከቡን ለችሎት አስታውቋል፡፡

የሙስና ጉዳዮች ዳሪክቶሬት ዐቃቤ ሕግ በበኩሉ ትርጉም የሚፈልጉ ሠነዶችን ገሚሱን አስተርጉሞ በተጠርጣሪዎች ላይ የሙስና ወንጀል ክስ ለመመስረት እንዲያስችለው የ15 ቀን ጊዜ እንዲሰጠው ፍርድ ቤቱን ጠይቋል፡፡ ተጠርጣሪዎቹ በበኩላቸው ትርጉም የሚፈልጉ ሠነዶችን ለማስተርጎም ተጨማሪ ጊዜ አይወስድም ሲሉ

የሙስና ወንጀል በመፈፀም... ወደ ገጽ 12 የዞረ

## ኪነ-ጥበብ

# እንመዘን!!

ይፈተሽ ይመዘን መንገዱ፣ የሰው ሁሉ አካሄዱ፤
ይመዝን ሚዘኑ ይሰላ ስሌቱ፣ ይተመን ይከፈል ይሰራ ውጤቱ፤
በገንዘብ በጥቅም ያልተደለለ፣ ለፍቶ ተግቶ ፍትህን የሰጠ፤
አገርና ህዝቡን ወዶ ያገለገለ፣ እራሱን ጊዜውን መስዋት ያደረገ፤
ልቦናው ህሊናው እጁ የነጻ፣ ምስጉን ታታሪ ለትውልድ አርአያ፤
አለ በሚዛኑ ተመዝኖ ያልቀለለ፣ ለአገር ለህዝቡ የታመነ፤
የጨከነ ለእውነት የተለየ፣ ከአመጽ፤
ያልተዘመረለት ያልተነገረለት፣ ተሸሽጎ ያለ የኖረ ለእውነት፤
ሙስና የታገለ በተግባር፣ ያልዋለ ከሌቦቹ ሰፈር፤
አንድ የሆነ አኗኗሩ፣ አነደበቱም ቃል ተግባሩ፤
አለ ተመዝኖ ያልቀለለ፣ ደግሞ እንዲህ አለ ተመዝኖ የቀለለ፤
ትውልድ አደህይቶ፣ ውስጡ ቆሸሾ እጁ ተጨማልቆ፤
የድሃ እንባ መቸ ሊገደው፣ መቸ ደንግጦ ልቡ ጨካኝ በገንዘብ ፍቅር ታውሮ፤
ለራሱ ለጥቅሙ ብቻ የሚኖር፣ ፈጣሪውን ያማይፈራ ሰውንም የማያፍር፤
አለ በሚዘኑ ተመዝኖ የቀለለ፣ ለአገሩ ለህዝቡ ያልታመነ!!
ጎተራውን እየሞላ እየነጠቀ ያከማቸ፣ በቃኝ  አይል እየጨመረ፤
የሀገር ሃብት እየመዘበረ፣ ሌላው ሲያለቅስ እየሳቀ፤
አለ በሚዛኑ ተመዝኖ የቀለለ!!
ደግሞ  የሚገርመው፣ እጅጉን የሚደንቀው፤
ተሰውሮ ገመናው ተደብቆ፣ እየሆነ ሰው መሳይ በሸንጎ ላዩ ታይቶ፤
ሲዘፈንለት ሲደነቅ ሲሞገስ ቃለት ሲደረደርለት፣ እንግዳው በሜዳ ተኮፍሶ፣
አዩ ዝና አዩ ስም ውስጡ ለቁስ ሆኖ ቀሎ ተገኘ ተፈትኖ፤
በሚዛኑ ተመዝኖ ደግሞ እንዲህ አለ፣ ተመዝኖ የቀለለ፤
ደሞዜ አይበቃ ኑሮም ተወደደ፣
ትንሽ ስጦታ ብቀበል ምናለ ሌብነት አይደለም ማንንም አልጎዳ፣
አለ አይደል እንዴ ሰርቆ ያካበተ፣ ብሎ የራሱን ሃጢያት ከሌላ አወዳድሮ፤
እራሱን ያጸደቀ ሌላውን ኮንኖ፣ የሙስና ትንሽ ትልቅ አለ ብሎ!!
ተመዝኖ በሚዛኑ ቀሎ ተገኘ ተመዝኖ፤
እንግዲያውስ እኛም እንመዘን የቱ ጋር ነን ሚና እንለይ፤
የማንን ገንዘብ ወሰድን፣ በማንስ ላይ ግፍ አደረግን፤
ማነን ገፋን ማነን ነጠቅን፣ ከማንስ ጋር ለጥቅም ተወዳጀን፤
በሚዛኑ ተመዝነን፣ ወደቅን ወይስ አለፍን?
የቱ ጋር ነን ሚና እንለይ፣ ከእንክርዳዱ ወይስ ከስንዴው ነን?!

በታሪኳግርማ

እንመዘን!!

# መልካም ዜጋ



ወ/ሮ ሠናይት በላይ ከኮርፖሬሽኑ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ከአቶ አቻ ደምሴ ዋንጫ፣ የምስክር ወረቀትና የገንዘብ ሽልማት ሲቀበሉ

## ታማኝነት በተግባር

**ከድር ጀማል**

ምንም ሳይደክሙ ተገቢ ያልሆነ ብልጽግና ለማግኘት ጥረት በሚደረግበት በዚህ በሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን የራስን ስሜት ገዝቶ በሀቀኝነትና በታማኝነት ደንበኞችን ማገልገል እጅግ የላቀ የሞራል ከፍታ ላይ የመድረስ ውጤት ነው።

በዚህ የላቀ የሞራል ከፍታ ደረጃ ከደረሱ የኢትዮጵያ ንግድ ሥራዎች ኮርፖሬሽን ሠራተኞች መካከል ወ/ሮ ሠናይት በላይ አንዷ ናቸው።

ወ/ሮ ሠናይት በላይ ነሐሴ 20 ቀን 2014 ዓ.ም ከጠዋቱ አራት ሰዓት በኮርፖሬሽኑ የአትክልትና ፍራፍሬ ንግድ ሥራ ዘርፍ ባልቻ ሆስፒታል አካባቢ በሚገኘው የሽያጭ ሥራቸውን በማከናወን ላይ እያሉ አንድ የድርጅቱ ተገልጋይ ግለሰብ በቾኮላ መጥተው አራት ኪሎ ግራም ብርቱካን ይገዙና ደረሰኝ ተቀብለው ይሄዳሉ።

የሽያጭ ሠራተኛዋ በሥራቸው ላይ እያሉ ድንገት ዞር ሲሉ አጠገባቸው ጋር ካለው የምርት ማሳያ (Products Display) ጠረጴዛ ላይ አንድ ትልቅ ቦርሳ ተቀምጦ ይመለከታሉ። በቦርሳው አጠገብ አገልግሎት የሚፈልጉ ሌሎች ተገልጋዮች በብዛት ቢኖሩም ቦርሳውን በዓይነ ቁራኛ እየተመለከቱ የተለመደ ተግባራቸው ማከናወናቸውን ይቀጥላሉ።

ይሁን እንጂ የነበሩ ተገልጋዮችን አስተናግደው ከጨረሱ በኋላ ቦርሳው ወደ ተቀመጠበት አቅጣጫ በድጋሚ ሲመለከቱ አሁንም ቦርሳው በነበረበት ቦታ ላይ ተቀምጦ ይመለከታሉ። ይህን ጊዜ የጥንቃቄ እርምጃ መውሰድ እንዳለባቸው በመገንዘብ ቦርሳውን ከነበረበት ሥፍራ አንስተው ወደ ውስጠኛው የሽያጭ መደብሩ ክፍል በማስቀመጥ መደበኛ ሥራቸውን መሥራት ይቀጥላሉ።

ሆኖም የቦርሳው ጉዳይ ስለከነከናቸው "ይህ ቦርሳ የማን ይሆን?" የሚል ጥያቄ አዕምሯቸውን ስላስጨነቀው ስለ ቦርሳው ባለቤት መረጃ ለማግኘት ብለው ቦርሳውን ከፈት አድርገው ወደ ውስጥ ሲመለከቱ በውስጡ በርካታ ገንዘቦች፣ ንብረቶችና ሰነዶች እንዳሉ አረጋገጡ። "ይህን ቦርሳ ጥሎት የሄደው የዘወትር ደንበኛዬ የነበረ ግለሰብ ሊሆን ይችላል" የሚል ጥርጣሬ ቢያድርባቸውም እርግጠኛ መሆን ግን አልቻሉም።

የንብረቱ ባለቤት ማንነትን ይበልጥ ለማረጋገጥ ፈልገው ቦርሳውን በድጋሚ ሲከፍቱ በውስጡ በርካታ የኢትዮጵያ ብር፤ የውጭ ሀገር ገንዘብ እና ሶስት የባንክ ሂሳብ ደብተሮች እንዲሁም የተለያዩ የህክምና ምርመራ ማስረጃዎችና ሌሎች ሰነዶች መኖራቸውን ያረጋግጣሉ።

በዚህ ሁሉ ሂደት ላይ እያሉ ድንገት አንድ በዕድሜው ጎልማሳ የሆነ ሰው በተጨነቀና በተደናገጠ ሁኔታ አጠገባቸው ቆሞ አገኙት። ይህን ሰው ከ4 ሰዓት በፊት አገልግሎት እንደሰጡት አስታወሱ።

"ወንድም! ምን ልርዳህ?" በሚል መልከ ፊት ፊቱን እያዩ ጥያቄቸውን በትህትና ያቀርባሉ። ለጊዜው ምንም ምርት እንደማይፈልግ ነግሯቸው ነገር ግን እዚህ ቦታ ላይ ቦርሳ ትቶ እንደሄደ ይገልጽላቸውና እሳቸው ቦርሳውን አይተውት እንደሆ ይጠይቃቸዋል።

የግለሰቡን ሁኔታ በትኩረት ተመልክተው ስለ ቦርሳው አጠቃላይ ሁኔታና ስለ ንብረቱ ባለቤት በተጨባጭ ማስረጃ ማግኘት ስለነበረባቸው፣ "ምን አይነት ቦርሳ ነው የጠፋብህ?" በማለት ጠየቁት። የቦርሳው ዓይነት እንዲሁም በውስጡ ያሉትን ነገሮች በተመለከተ አንድ በአንድ ዘርዝሮ ነገራቸው።

ወ/ሮ ሠናይት የንብረቱ ባለቤት መሆኑን በእርግጠኝነት ለማወቅ ፈልገው ስለ ራሱ እንዲነግራቸው ጠየቁት። "ስሜ እንግዳዬ መኮንን እባላለሁ፤ ባለቤቴ ታማ ባልቻ ሆስፒታል ኦፐራሲዮን ልትሆን በመተኛቷ የምይዘውና የምጨብጠው ነገር ጠፍቶብኝ ነበር። ከዚህ የሽያጭ መደብር ፍራፍሬ ገዝቼ መሄዴን እንጂ ምን እንደያዝኩ እንኳን እርግጠኛ አልነበርኩም፤ ቦርሳው ትዝ ያለኝ ባለቤቴ ለህክምናው ማስያዣ ገንዘብ ስትጠይቀኝ ነው። በዚህ ጭንቀት ውስጥ በመሆኔ ነው ቦርሳው ባስቀመጥኩበት እዚህ ሥፍራ ትቼው የሄድኩት፤ ከዚህም በተጨማሪ ስለ እኔ ማንነት ለማወቅ ቦርሳው ውስጥ ባለው ማስረጃ ማረጋገጥ ትችያለሽ" በማለት ምላሽ ሰጣቸው።

የሽያጭ ሠራተኛዋ ለአቶ እንግዳዬ ባቀረቡት የምርመራ ጥያቄ መሠረት የተሟላ ምላሽ በማግኘታቸው ንብረቱን ማለትም ቦርሳው የእሳቸው መሆኑን በውስጡ ባለው መረጃ መሠረት በተጨባጭ ማስረጃ ማረጋገጥ በመቻላቸው ቦርሳውን ከነበረበት ሥፍራ አንስተው ለባለቤቱ አስረከቡት።

ቦርሳውን ከተረከቡ በኋላ አቶ እንግዳዬ፣ "በቦርሳው ውስጥ ለህክምና አገልግሎት የያዝኩት ከ19 ሺህ በላይ የኢትዮጵያ ብር እና 250 የአሜሪካን ዶላር ከዚህም በተጨማሪ በጣም ለህይወታችን አስፈላጊና ጠቃሚ የሆኑ የተለያዩ መረጃዎች የያዘ ቦርሳ ነው። በነገራችን ላይ የሽያጭ ሠራተኛዋን ስለ ቦርሳው ስጠይቃት ንብረቱ እንደነበረ አገኘዋለሁ ብዬ አላሰብኩም ነበር። በተለይ የሽያጭ ሠራተኛዋ መጠየቅ የሚገባትን የማጣሪያ ምርመራ ከጠየቀችኝ በኋላ ቦርሳውን ካስቀመጠችበት አንስታ ስትሰጠኝ በፍጹም ማመን አልቻልኩም፤ በእርግጥ የሰው ሀቅ የትም አያደርስም፤ ነገር ግን በሠራተኛዋ ላይ የተመለከትኩት ታማኝነት በጣም የሚገርም ነገር ነው" በማለት ተናግረዋል።

በመጨረሻም አቶ እንግዳዬ መኮንን ኮርፖሬሽን ድረስ በመሄድ ወ/ሮ ሠናይት በላይ ለፈጸሙት መልካም ተግባር የሚመለከተው አካል ጋር ቀርበው ምስጋና አቅርበዋል።

በአጠቃላይ ወ/ሮ ሠናይት በላይ የሥነምግባር መርህዎች አንዱን የሆነውን የታማኝነት መርህ በተግባር በማሳየታቸው፤ ለኮርፖሬሽኑ የገጽታ ግንባታ ከፍተኛ ሚና በመጫወታቸው፤ ጊዜያዊ ጥቅም ሳያታልላቸው ለሙያቸው ታማኝና ቅን በመሆን ለሌሎች ሠራተኞች አርዓያነት ያለው ተግባር በመፈጸማቸው የኢትዮጵያ የንግድ ሥራዎች ኮርፖሬሽን የማኔጅመንት ቡድን ተነጋግሮ በ2015 ዓ.ም በኮርፖሬሽን ደረጃ በተከበረው ዓለም አቀፍ የፀረ-ሙስና ቀን በዓል ሁሉም ሠራተኞች በተገኙበት የዕውቅና የምስክር ወረቀት፣ዋንጫ እና የገንዘብ ሽልማት ተበርክቶላቸዋል።

## የሙስና ወንጀል በመፈፀም ምርመራ...

ተከራክረዋል። የቤተሰብ አስተዳዳሪ መሆናቸውን እና ቋሚ አድራሻ እንዳላቸው ገልጸው የዋስትና መብታቸው እንዲከበር ጠይቀዋል።

ዐቃቤ ሕግ በበኩሉ እንዲሸሽ በተደረገው የአሜሪካ ዶላር በሀገሪቱ ላይ ጉዳት መድረሱን ጠቅሷል። ከ10 ዓመት በላይ በሚያስቀጣ አንቀጽ የሚከሰሱ መሆኑን ገልጾ የዋስትና ጥያቄያቸውን ተቃውሞ ተከራክሯል።

ክርክሩን የተከታተለው የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ልደታ ምድብ የጊዜ ቀጠሮ ችሎት የተጠርጣሪዎቹ የዋስትና ጥያቄ ውድቅ በማድረግ ዐቃቤ ሕግ ከጠየቀው 15 ቀናት ውስጥ 10 ቀን የክስ መመስረቻ ጊዜ መፍቀድ ችሏል።

ሌላው መረጃ ደግሞ በአዲስ አበባ ኤርፖርት የኮቪድ 19 ወረርሽኝ ስርጭትን ክትትል እና ቁጥጥር እንዲያደርጉ የተመደቡ የህብረተሰብ ጤና ኢንስትቲዩት ሰራተኞች ከውጭ ገቢ መንገደኞች የኮንትሮባንድ እቃን በመረከብ እና ደብቀው ለማሳለፍ ሲሞክሩ እጅ ከፍንጅ መያዝ መቻላቸውን ያመለክታል፡፡

የጉምሩክ ኮሚሽን ኤርፖርት ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት ጥር 12 እና 13/2015 ዓ.ም ባደረገው ክትትል ከመንግስት የተሰጣቸውን ኃላፊነት ሽፋን በማድረግ 42 ዘመናዊ የእጅ ስልኮች እና በርካታ የስማርት ስልክ ቦርድ ስክሪኖችን በቦርሳ በመደበቅ ይዘው ለመውጣት የሞከሩ ሁለት የኢንስቲትቱ ሰራተኞች በቁጥጥር ስር አውሏል።

በአዲስ አበባ ኤርፖርት ህገወጥ የገንዘብ ዝውውር፣ የከበሩ ማዕድናት፣ የአደንዛዥ እጽ ዝውውር እና ሌሎች መሰል ወንጀሎች በተደጋጋሚ እየተስተዋሉ በመሆኑ ተቋማትን በመወከል የሴኩሪቲ መግቢያ ፈቃድ መታወቂያ ይዘው በሚንቀሳቀሱ አካላት ላይ ጉምሩክ ኮሚሽን ከወትሮው በተለየ ጥብቅ ፍተሻ እንደሚያደርግ ያስታወቀ ሲሆን፤ ኮሚሽኑ በዚህ የህግ ማስከበር ስራ ላይ ለተሳተፉ ለአዲስ አበባ ኤርፖርት ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት አመራሮች እና ሰራተኞች ምስጋና አቅርቧል፡፡

የኮንትሮባንድ እና ህገወጥ ንግድ የአፈጻጸም ስልቱ ተለዋዋጭ በመሆኑ ድርጊቱን ለመግታትና በሀገር ኢኮኖሚ የሚያሳድረውን አሉታዊ ተጽእኖ ለመከላከል ጉምሩክ ኮሚሽን ብቻ የሚያደርገው እንቅስቃሴ በቂ ባለመሆኑ ሁሉም ባላድርሻ አካላትና ህብረተሰቡ የበኩሉን ድርሻ እንዲወጣ ጥሪ መቅረቡን የጉምሩክ ኮሚሽን መረጃ አመላክቷል፡፡

በመጨረሻም በቀድሞው የአቪየሽን ሴኪዩሪቲ ዘርፍ የክፍል ዋና ኃላፊ አቶ ደረጀ መንግስቱ 8 ነጥብ 9 ኪሎ ግራም ኮኬይን ዕፅ ለግል ጥቅሙ አውሏል ተብሎ በቀረበበት የሙስና ወንጀል ክስ ላይ ምስክር ተሰምቷል። አቶ ደረጀ መንግስቱ በቦሌ ዓለም አቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ በመንገደኛ የተያዘ 8 ነጥብ 9 ኪሎ ግራም ኮኬይን ዕፅን ለግል ጥቅሙ አውሏል ተብሎ በቀረበበት የሙስና ወንጀል ክስ ላይ የዐቃቤ ህግ አራት ምስክሮች ተሰምተዋል። የምስክሮችን ቃል ያዳመጠው የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ልደታ ምድብ 3ኛ የሙስና ጉዳዮች ወንጀል ችሎት ነው።

ተከሳሹ ሰኔ 29 ቀን 2014 ዓ.ም በቦሌ ዓለም አቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ እንዳይዘዋወርና ጥቅም ላይ እንዳይውል የተከለከለ 96 ኪሎ ግራም ኮኬይን ዕፅ ከአንድ መንገደኛ ላይ በአደገኛ ዕፅ ቁጥጥር ባለሙያዎች መያዙ የሚታወስ ሲሆን፤ ከተያዘ በኋላም ተከሳሹ ለፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን ወንጀል መከላከል ጠቅላይ መምሪያ የአደገኛ ዕፅ ቁጥጥርና ፀረ ፈንጅ መምሪያ ዕፁን ሲያስረክብ ከ96 ኪሎ ግራም ዕፅ ላይ 8 ነጥብ 9 ኪሎ ግራም ኮኬይን ቀንሶ ለግል ጥቅሙ አውሏል በሚል ህዳር 12 ቀን 2015 ዓ.ም ስልጣን ያለአግባብ መገልገል ከባድ የሙስና ወንጀል ክስ ተመስርቶበት ነበር። ተከሳሹ ክሱ ከደረሰውና በችሎት በንባብ ከተሰማ በኋላ ክሱ እንዲሻሻልለት በጽሁፍ አቅርቦ የነበር ሲሆን፣ ፍርድ ቤቱም የተከሳሹን የክስ መቃወሚያ ጥያቄና እና ዐቃቤ ህግ ክሱ ሊሻሻል አይገባም ሲል ያቀረበውን መልስ መርምሮ ተከሳሹ ያቀረበው የክስ መቃወሚያ ክሱን ለማሻሻል የሚያስችል የህግ መሰረት ያለው ጥያቄ አይደለም ሲል ውድቅ አድርጎታል። የክስ መቃወሚያው ውድቅ ከተደረገ በኋላ ተከሳሹ ወንጀሉን አልፈጸምኩም በማለት የእምነት ክህደት ቃሉን ሰጥቷል።

በተጨማሪም በየችሎት ቀጠሮ ወቅት ዐቃቤ ህግ አራት የሙያ ምስክሮችን አስቀርቦ በወንጀሉ አፈጻጸም ዙሪያ የምስክርት ቃላቸው እንዲሰማ ያደረገ ሲሆን ምስክሮችን ቃል ያዳመጠው ፍርድ ቤቱ መርምሮ ብይን ለመስጠት ለየካቲት 20 ቀን 2015 ዓ.ም ተለዋጭ ቀጠሮ መስጠቱን ያገኘነው መረጃ ያመለክታል።

በቀጣይ የፀረ-ሙስና ጋዜጣ ዕትም በሂደት ላይ ያሉ የሙስና ወጀሎችን ተከታትለን ለአንባቢያን የምናደርስ ይሆናል፡፡